
ማነው ተጠያቂው?

ካህኑ ወይስ ሕዝቡ?



በቀሲስ መዘምር ወ/ሩፋኤል

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

2004 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Reserved

ምስጋና

- ከሁሉም በፊት ይህን መጽሐፍ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ ለአማልእክት አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው።
- የመጽሐፉን የቃላት ፍሰት በማስተካከል (በአርትዖት) ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው የተባበሩኝን የቤተክርስቲያን ልጆች ከልብ አመሰግናለሁ።

<u>የመጽሐፉ አዘጋጅ አድራሻ</u>

ቀሲስ መዘምር ወ/ሩፋኤል

የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ

ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ

ሞባይል፡ 0911-31-68-93

ፖስታ ሣ.ቁ. 80947

ስጦታ

ከ _____

ለ _____

ቀን _____

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ 5

ምዕራፍ አንድ

1. "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል" 7
   - 1.1. ሕይወት የሚገኝበት እውቀት.....7
   - 1.2. እናስተውል 8
     - 1.2.1. "ለማያስተውሉ ዕዳ አለብኝ" 9
     - 1.2.2. ወደማያስተውለው ሕዝብ ማን ይላክ?.....10
     - 1.2.3. ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ 10
   - 1.3. የእረኞች ጥፋት 21
   - 1.4. ቃሉን ማን ያስተምር?.....23
   - 1.5. በቤተ ክርስቲያን ያሉ ችግሮች.....24

ምዕራፍ ሁለት

2. ጥፋት ምንድን ነው? 26
   - 2.1. የጥፋት ልጅ 27
   - 2.2. እግዚአብሔር የሰውን ጥፋት አይፈልግም.....28
   - 2.3. መጥፋት ወይም አለመጥፋት 29

ምዕራፍ ሦስት

3. እግዚአብሔርን እወቅ 30
   - 3.1. ከመሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ.....31
   - 3.2. እውቀት የጎደለበት የዮፍታሔ መሥዋዕት.....32

እንደ ድፍረት አይቆጠረብኝና በዘመናችን በአንዳንድ ካህናት ምክንያት የጠፉ ሕዝቦች ቁጥር እጅግ ብዙ ነው። ይህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለቤተ ክርስቲያናችን ጉዳት ነው። ሕዝቡ ተስፋ የጣለባቸው ካህናት (እረኞች) ሃይማኖታዊ ኀላፊነታቸውን በተገቢው ሁኔታ ባልተወጡ ቁጥር ሕዝቡም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ደካማና ተጎጂ እየሆነ መምጣቱ የማይቀር ነው። ከብሉይ ኪዳን ሕዝብ የምናስተውለውም ይህን ምክንያትና ውጤት ነው።

በትክክል የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነ አገልጋይ ከሁሉ በፊት ለጠፋው ሕዝብ ያዝናል፣ የሚያስፈልገውንም ትምህርት ያስተምራል። በላቀ አገልግሎቱ ስለሚታወቀው መጥመቀ መለኮት ዮሐንስ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ ሲመሰክር "የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ" ይላል (ሉቃ1÷77)።

መዳን በሰዎች ሕይወት ነግሦ እንዲኖር እንደ ውሃ ልክ ሆኖ የሚያገለግለው መንፈሳዊ እውቀት ቃለ እግዚአብሔር በመሆኑ ዛሬም የቀደሙት ካህናትና ሕዝብ ታሪክ ለሁላችንም ትምህርት ይሆነን ዘንድ በእነርሱ ታሪክ የእኛን ሕይወት ለመፈተሽና ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ለማድረግ ይህን አነስተኛ መጽሐፍ በፈቃደ እግዚአብሔር አዘጋጅቼአለሁ።

መልካም ንባብ ይሁንላችሁ

ከአዘጋጁ።

ምዕራፍ አንድ

1. "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል"

የእግዚአብሔር ቃል የምግብ ያህል ለሰው ልጆች ሕይወት ነው (ዘዳ. 8÷3፤ ማቴ. 4÷4)። ያለ እንጀራ በሕይወት መኖር እንደማይቻል ሁሉ የቃሉን እውቀት ማጣትም እንደዚያው ነውና "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል" ይላል እግዚአብሔር (ሆሴ.4÷6)። አለማወቅና ስንፍና ካለ ጥፋት አብሮ አለ (ምሳ.1÷29-32)። ቃሉን ስናውቅ እግዚብሔርን እናውቀዋለን÷ እግዚአብሔርን ስናውቀው ደግሞ ለእርሱ እየተገዛን በሕይወት እንኖራለን።

1.1. ሕይወት የሚገኝበት እውቀት

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።" (ዮሐ. 17÷3)። ሕይወት የሚገኝበት የቃሉ እውቀት ለሁሉም አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም ክርስቶስ ነው (ፊል.3÷8-9)። ክርስቶስን በቃሉ መሠረት ካወቅን የተሰወረው የእግዚአብሔር ምስጢርና ጥበብ ሁሉ በእርሱ ይታወቃል (ቆላ.2÷2-3)። "ቃል" እግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ሲሆን÷ በነቢያትና በሐዋርያት የተጻፈው (መጽሐፍ ቅዱስ) የእግዚአብሔር ቃል ይባላል (ማቴ.4÷4፤ 2ጴጥ.1÷20-21)።

ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር በነቢያት በኩል በልዩ ልዩ መንገድ ተናግሮአል፤ ወይም ቃሉን አስተላልፎአል (ዕብ.1÷1)። ይሁን እንጂ በነቢያት ሲነገር የነበረው የእግዚአብሔር ቃል÷ ሰውን ሁሉ ወደ ክርስቶስ ለማድረስ ነበርና። በዘመኑ መጨረሻ ላይ ግን በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረ (ቁ.2)።

በነቢያት የተነገራቸውን ቃል ባለመታዘዛቸው ምክንያት እንደ ጠፉ "ቃል" በተባለ በክርስቶስ የተነገረውን የእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ የማትሰማ ነፍስም ትጠፋለች (ዘዳ.18÷17-19፤ የሐዋ.ሥ.3÷22-23)። ቃሉን የሚሰማ ደግሞ ለዘላለም በሕይወት ይኖራል (ዮሐ. 5÷24)።

1.2. እናስተውል

አለማስተዋል ያለበት ሕይወት ከፍተኛ ጉዳት አለበት። በነቢዩ ሆሴዕ በኩል ከተነገሩት ወቀሣዎች መካከል የሕዝቡ አስተዋይ አለመሆን አንዱ ችግር ነበር። በፈጣሪያቸው ላይ የሚፈጽሙአቸው በርካታ ኃጢአቶች ነበሩ። ማስተዋል የሚባል ነገርም በፍጹም አልነበራቸውም። ወደ ጥፋት የሚመራቸውም አለማስተዋላቸው ነበር። ስለዚህ "የማያስተውል ሕዝብ ይገለበጣል።" አለ (ሆሴ. 4÷14)።

"ይህን ነገር የሚያስተውል ጠቢብ÷ የሚያውቃትም አስተዋይ ማን ነው? የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው÷ጻድቃንም ይሄዱበታል፤ ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል።" (14÷9)። የእግዚአብሔር ሰው ኢዮብ ደግሞ "ማስተዋል" ማለት ከኃጢአት መራቅ ማለት እንደሆነ ይገልጻል (ኢዮ. 28÷28)።

በእግዚአብሔር ታምኖ በእርሱ ላይ የሚደገፍ እንጂ በራሱ ማስተዋል የሚደገፍ ሰው የትም አይደርስም። ይልቁንም ማስተዋል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። (ምሳ. 3÷5-10)። የሰው ማስተዋል ብቻውን ትርጉም አልባ ነው። ለጌታ ደቀ መዛሙርቱ መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ ጌታ አእምሮአቸውን እንደ ከፈተላቸው

እናነባለን (ሉቃ. 24÷45)። ማስተዋል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ እንደሆነ አሁንም ማስተዋል አለብን።

ጌታችን ስለ መንግሥተ ሰማያት በብዙ ምሳሌ ባስተማረበት በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ዐሥራ ሶስት ላይ ደቀ መዛሙርቱን "ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል÷ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።" ሲል ስለ መንግሥቱ ቃል ማስተዋል የተሰጣቸውና ያልተሰጣቸው መኖራቸውን በዝርዝር ገልጦአል (ቁ.11-23)።

ከእግዚአብሔር የሆነው ማስተዋል ጥበበኞችና አስተዋዮች የሚባሉት አለን ከሚሉት ማስተዋል ሁሉ በላይ ነው (ማቴ.11÷25)። የእኔ ከምንለው ማስተዋል ይልቅ የአምላካችን የሆነውን ጥልቅ ማስተ÷ል ልንናፍቀው ይገባል። ያን ጊዜ በእውነት አስተዋዮች እንሆናለን (1ቆሮ. 2÷12-13)።

1.2.1. "ለማያስተውሉ ዕዳ አለብኝ"

ለእግዚአብሔር ሕዝብና አገልጋዮች መንፈሳዊውን እውነታ አለማስተዋልና አለማወቅ ጉዳቱ የላቀ ነው። "እስራኤል ግን አላወቀም ሕዝቤም አላስተዋለም።" (ኢሳ.1÷3) ሲል እግዚአብሔር የሕዝቡን እውቀትና ማስተዋል ማነስ የገለጸበት እውነት አለ። ለዚህ ደግሞ ሕዝቡን ለማገልገል ኃላፊነቱን የወሰዱት ዕዳ እንዳለባቸው ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ሐዋርያው ማንኛውም ሰው ቢሆን የወንጌልን ቃል ሰምቶ ወደ ማስተዋል እንዲደርስ÷ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ይፈልጋል። ለተማረውም ላልተማረውም÷ አይሁዳዊም ይሁን አረማዊ÷

ወንጌልን የመስበክ ኃላፊነት እንዳለበት ነው የተናገረው። ያለ ወንጌል ብርሃን መንፈሳዊ ማስተዋል አይገኝምና። "ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ ... ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።" በማለት ለማያስተውለው ሕዝብ የወንጌልን ቃል ለመዝራት ቆርጦ መነሣቱን ያሳየናል (ሮሜ 1÷14-15፤ 1ቆሮ. 9÷16 ይመለክቱ)።

1.2.2. "ወደማያስተውለው ሕዝብ ማን ይላክ?"

እግዚአብሔር÷ ሕዝቡ ባለማወቅ ሕይወቱ እንደጠፋ እንዲቀር አይፈልግም፤ ይልቁንም መንፈሳዊ ኃላፊነቱን አውቆ የሚላክና ባለማስተዋል የጠፉትን ሕዝብ ወደ አምላካቸው የሚመልስ ታማኝ መልክተኛ ይፈልጋል።

በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ አንድ ላይ ተመዝግቦ እንደምናገኘው እግዚአብሔር አምላክ የጠፋውን ሕዝብ ስለ ጥፋቱ ነገሮት የሚመልሰውን መልክተኛ በመፈለግ "ማንን አልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?" የሚለውን የእግዚአብሔርን ድምፅ የሰማው ነቢዩ ኢሳይያስ "እነሆኝ÷ እኔን ላከኝ" ብሎታል (ኢሳ.6÷8)። እግዚአብሔርም "ሂድ÷ይህን ሕዝብ፡- መስማትን ትሰማላችሁ፤ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው" አለው (ቁ.9)። በዘመናችንም ብዙ ክርስቲያኖች ቃሉን እየሰሙ ማስተዋል ግን አቅቷቸው ይታያል። ወደዚህ ወደማያስተውለው ሕዝብ የእግዚአብሔር ታማኝ መልክተኛ ሆኖ የሚሄድ አገልጋይ መጥፋቱ ደግሞ ከሁሉም በላይ ያሳዝናል።

1.2.3. "ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?"

"እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና" (ዮሐ.3÷34) እንደ ተባለው÷ ተልዕኮውን የሚያውቅ÷ እግዚአብሔር

የላከው መልክተኛ እንጂ÷ ያልተላከ መልክተኛ ከሆነ ተልዕኮውን መወጣት አይችልም።

ለማመንና እግዚአብሔርንም ለማወቅ ስብከት አስፈላጊ መሆኑን የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ÷ "ያለ ሰባኪ እንዴት ይሰማሉ?" ... ካልተላኩስ እንዴት ይሰብካሉ?" ሲል ሰው÷ከጥፋትና ከሞት የሚድንበትን ወንጌል የሚሰብኩ መልክተኞች ከሌሉ ቃሉን መስማትም ሆነ መዳን እንደማይኖር ገልጾአል (ሮሜ 10÷14-17 ይመልከቱ)። የተላከ መልክተኛ (አገልጋይ) የምሥራች የተባለውን ወንጌል ይሰብካል የተሰበከለትን ወንጌል በማስተዋል የሰማም በእምነት የጌታውን ስም ይጠራል የመንግሥቱ ወራሽም ይሆናል። ከዚህ አንጻር ምን እያደረግን ነው?

ሀ) "ወንጌል እናሳልማለን እንጂ ወንጌል አላስተማርንም"

ቃለ ወንጌልን አለመማር÷ አለመስማት÷ አለማንበብ÷ አለማስተዋልና አለመታዘዝ ካለ ምንጊዜም ቢሆን የመዳናችንን መንገድ እየዘጋነው መሆኑን ማወቅ ይገባናል (ዮሐ.8÷43-51፤ ማቴ.7÷24-25፤ ዮሐ.5÷24)። የወንጌል ዓላማው በሰዎች ልብ ተቀምጦ ሰዎች እንዲጠቀሙበት እንጂ እንዲሰሙት ብቻ አይደለም። በቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓተ አምልኮት መጻሕፍት "የከበረ የወንጌልን ቃል ሰምተን እንሠራ ዘንድ" "ክቡር የሚሆን የወንጌልን ቃል በልቡናችን ትጽፍ ዘንድ" ወዘተ ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን (ሥርዓተ ቅዳሴ)።

አንድ አባት ካህናትን ሲያስተምሩ "ሕዝቡን ወንጌል ማሳለም እንጂ ወንጌልን አላስተማርንም፤ በእግዚአብሔር ቃል እጦት ለሚጠፋው ሕዝብ እያንዳንዳችን ተጠያቂዎች ነን።" ማለታቸውን

አስታውሳለሁ። በእርግጥ የተነበበውን ቅዱስ ወንጌል መሳለሙ ለቃሉ ክብር ከመስጠት አኳያ ስለሆነ የሚነቀፍ ባይሆንም÷ የሰማነው ቃለ ወንጌልና የተሳለምነው ወንጌል በልባችን ተጽፎ የማይቀመጥና መሳለም ብቻ ከሆነ መምህሩ እንዳሉት ከጥፋት አያድንም።

ብዙ ሰው ቅዱስ ወንጌልን ይሳለማል÷ መስቀሉን ይሳለማል÷ ቤተክርስቲያንን ይሳለማል÷ እነዚህን መሠረታዊያን የክርስትና ሕይወት ምስጢሮችን በማስተማር በአፋ የሚሰመውን ወንጌል በልቡም እንዲያስቀምጠው የማድረግ ኃላፊነት አለብን።

በአንድ ወቅት በየመንገዱ ሳይቀር የአባቶችን መስቀል የተሳለመ÷ በየጠዋቱ ቤተ ክርስቲያን ሳይሳለሙ የማይውሉ የነበሩ÷ ወንጌሉን ተሳልመው ጸበሉን ጠጥተው የመሄድ ልምድ የነበራቸው ብዙዎች÷ ዛሬ በዚያው ሕይወት የሉም። ለዚህ የተለያዩ ችግሮች አይኖሩም ባይባልም የወንጌል እውቀት ላጣው ሕዝብ የወንጌልን እውነት አለማስተማራችን ግን አንዱ ችግር መሆኑን በርካታዎች እንደሚስማሙበት አያጠራጥርም። "ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።" (ራእ.1÷3)።

ለ) "አባ÷ጌታን ስለተቀበልኩ አይድከሙ"

ጉዳዩ አንዳንዶችን ብዙ ባያስደንቅም የአንዳንዶች መነጋገሪያ አጀንዳ ግን ሆኖ ነበር። ሴትየዋ ረጅም ዓመታት ከነበሩበት የእምነት ተቋም ወደ ሌላው የእምነት ተቋም እንደሄዱ የሰማ ሁሉ "ሃይማኖትዋን ቀየረች" እያለ ወሬውን አናፈሰው።

ከዚህ በኋላ ነበር÷ የተወሰኑ የሃይማኖት አባቶች "በዚህ ዕድሜያቸውማ ሃይማኖታቸውን መቀየር የለባቸውም" በሚል ቁጭት

ስማስተማርና ለመምከር ወደ ሴትየዋ ያመሩት። የሴትየዋ መልስ ግን "አባ÷ጌታን ስለተቀበልኩ አይድከሙ፤ እስካሁን በጨለማ ኖሬአለሁ..." የሚል ነበር። "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" ዓይነት የሆነው የአባቶች ሂደትም በዚሁ ሁኔታ ማክተሙን በአንድ አካባቢ የተከሠተውን ይህን ሃይማኖታዊ ጉዳይ አንድ ሰው አጫውቶኛል።

እንደ ምሳሌ አነሣሁ እንጂ በዘመናችን እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮችን መስማትና ማየት አዲስ አይደለም። የሃይማኖት አባቶች ሰዎች የሚድኑበትን ቃለ ወንጌል በተገቢው መንገድ አስተምረናቸዋል ወይ? የሚለው ግን በጣም ሊሠመርበት ይገባል።

ሐ) "ኃጢአት ያለበት ሰው እያለ ኃጢአት የሌለበት ግድግዳ ምን አደረገ?"

በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የማኅበረ ካህናት ስብሰባና አገልግሎት ዙሪያ በተደረገ ውይይት ከበላይ አካል የመጡ አባት ሲናገሩ÷ ካህናት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና ማወቅ ሕዝቡን ማስተማር እንዳለባቸው ከገለጹ በኋላ÷ "ኃጢአት ያለበት ሰው እያለ÷ ኃጢአት የሌለበት ግድግዳ ምን አደረገ? እንደ እሳት አደጋ ውኃ እየረጨን ከመምጣት ይልቅ÷ ኃጢአት ያለበትን ሰው ለምንድነው አስተምረን የማንመልሰው? ..." ሲሉ በድፍረት እውነታውን ተናገሩ። "የልቡን ሲነግሩት የከረከሩትን ያህል ይስቃል" እንደሚባለው ይህ በጊዜው ተሰብሳቢውን ማኅበረ ካህናት ያስፈገገ ንግግር ነበር። እኚህ አባት ካህኑ የምዕመኑን ያህል እንኳ መጽሐፍ ገዝቶ የማንበብ ልምድ እንደሌለውም ገልጸው ነበር።

ቃለ እግዚአብሔር ሳይተነፍሱ÷ምክርና ትምህርትም ሳይለግሱ ጸበል ብቻ ረጭተው የሚመለሱት "የሃይማኖት አባቶች"

(ካህናት) በቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል፤ የብዙ ሕዝብ የነፍስ አባቶችም ናቸው። ይህ ሂደት በዚሁ ከቀጠለ አርቶዶክሳዊውን ምዕመን በያዘው እምነት እስከ መቼ ማቆየት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ ቅን የእምነቱ ተከታይ ሁሉ ሊያስብበትና ሊመልሰው ይገባል።

አብዛኞቻችን ጸበል ለመርጨት ስንሄድ የእውቀትና የሕይወት መሠረት የሆነውንና እያንዳንዱን ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን የምሕረት ቃል (የምሥራች) ይዘን ስለማንሄድ÷ ብዙዎቹ ምዕመናን ለቃሉ ቦታ የሌላቸውና ጸበል ብቻ ፈላጊ እንዲሆኑ አድርገናል።

በየሰፈሩ በቤታቸው በራፍ በጠርሙሽ አሊያም በላስቲክ የጸበል ውኃ ያንጠለጠሉ ሞልተዋል። ጸበሉን ለሚቀድሰው÷ ሕይወትንም ደግፎ ለሚይዘው ለሕያው ቃሉ ግን ቦታ የላቸውም። ነብየ እግዚአብሔር ኤርምያስ "ለሕዝብ ሁሉ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል÷ ቃሌን እንዳይሰሙ አንገታቸውን አደንድነዋል" (ኤር.19÷15) እንዳለው አብዛኛው ሕዝባችን ለሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ያለውን ፍቅር ያህል ቃሉን የማወቅና የመስማት ፍቅር አይታይበትም። የቃሉ ፍቅር ቢኖረው ክርስትና ምን ያህል ያድግ እንደነበር ለሁላችንም ግልጽ ነው።

መ) አነጋጋሪዎቹ የዘመናችን ጸበል አጥማቂዎች

ከፍ ብለን እንዳየነው በአሁኑ ጊዜ ጸበል በሕዝቡም በካህኑም ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል። በተለይም ሕዝቡ ለጸበል ያለውን ፍቅር በማየት በየጊዜው÷ በየአከባቢው ጸበል አጥማቂ ሆነው የተነሡትን ሰዎች ብዛት ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።

ምንም ይሁን ምን ጸበል አጥማቂ መጣ (አለ) ከተባለ ወደዚያ የሚጎርፈውን ሕዝብ ቤቱ ይቁጠረው። ጸበል አጥማቂ ወሬ በሰሙ ቁጥር ከቦታ ወደ ቦታ እንደተንከራተቱ የሚኖሩ ወገኖች አያሌ ናቸው። ገንዘብ ላይ ያተኮሩና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጣሱ÷ ለተጠማቂውም ፈውስ የማያስገኙ÷ ይልቁንም ጭንቀትና ዕብደት ውስጥ የሚከቱ አጥማቂዎች እየበዙ የመምጣታቸው ነገር ብዙ አነጋጋሪ የሆነበት ዘመን ላይ እንገኛለን።

ሰዎችን ካሰባቸው ደዌ ሥጋ መፈወስና ከአጋንንት አስራት ነጻ ማውጣት ሳይሆን ማጪጪህ ብቻ የሆነው የጸበል አጥማቂነት ነገር ያሳሰባቸው የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ለአድባራቱና ለገዳማቱ ባስተላለፉት መመሪያ "... በማጥመቅ ሂደት ላይ የተከሠቱ የኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/የባህልና የሥርዓት ያልሆኑ አባባሎችና አሠራሮች መኖራቸውን ከራሳቸው (ከተጠማቂዎቹ) አንደበት ለመረዳት ችለናል። ለምሳሌ በተሰጣቸው ጸጋ በሞባይል ስልክ ርኩስ መንፈስ እንደሚያስለቅቁ የሚያጠምቁአቸው ምእመናን የተፈጠረባቸውን የመንፈስ መዛባት ከራሳቸው አንደበት ሰምተናል። ይህም ከቤተክርስቲያን ቀኖና ውጪ የሆነ ባህልና አባባል ነው። ..." ሲሉ ያለ ሥልጣነ ክህነትና ቀኖና ቤተክርስቲያንን በጣሰ ሁኔታ የሚፈጸመውን አጥማቂነት አስመልክተው በጻፉት ደብዳቤ ገልጸዋል።

አንዳንዱ በጸበል አጥማቂነት÷ ሌላው በሌላ መልኩ የምእመናንን የውስጥ ብሶት እየነካኩና ያለ ፈውስ÷ ያለ ዕረፍት÷ ሽክም ብቻ እየጫኑ የሚኖሩ ብዙ ናቸው። የሰሙትና ያዩት ሁሉ እውነት የሚመስላቸው በእውቀት እጦት እንደባዘኑ የሚኖሩም ቁጥራቸው የትየሌሌ ነው።

ሠ)ማኅበሮቻችንስ ምን ይመስላሉ?

ምዕመናን የክርስትና እምነታቸውን ከሚገልጡባቸው መንገዶች አንዱ በማኅበር መሰባሰባቸው ነው። ይህ መሰባሰብ በሐዋርያት ዘመን (በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች) ይከናወን ነበር። ሲሰባሰቡ የሐዋርያትን ትምህርት÷ ጸሎትና እንጀራንም አብሮ መቁረስ በኅብረታቸው ውስጥ የሚፈጽሙአቸው ዋናዎቹ መንፈሳዊያን ተግባራት ነበሩ (የሐዋ.ሥ.2÷41-42)።

ማኅበር መልካም ሆኖ እያለ የዘመናችን አብዛኞቹ መንፈሳዊያን ማኅበራት ቃለ ወንጌል ያልዞረባቸው÷ መብልና መጠጥ ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆናቸው ያሳዝናል። የቤተክርስቲያኒቱ ደንብ በሆነው ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፰ "በሰንበቴና በገዝክር ጽዋዕ ሳቢያ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ... አምሳለ ታቦት ጃንጥላ ይዘውና መብራት አብርተው በየመንደሩና በየመንገዱ በሚዘዋወሩት ካህናትና ምእመናን ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ..." ማድረግ እንደሚገባ ይደነግጋል። መመሪያውን በመተግበር ፈንታ ይባስ ብሎ በስበሮና በዕልልታ መታጀብ ከጀመረ ውሉ አድሮአል። አብዛኞቹ ካህናትም ጸበልዋን ረጭተው÷ ከምትበላዋና ከምትጠጣዋ ተቋድሰው ይሄዳሉ እንጂ የማኅበርን እውነተኛ ዓላማ የሚገልጹ አይደሉም።

ሕዝባችን ምን ያህል ሃይማኖት ለበስ÷ መንፈሳዊ መሰል በሆኑ ልማዳዊ ነገሮች እየተዋጠና ከቃለ እግዚአብሔር እውቀት እየወጣ መሆኑንና ቤተ ክርስቲያን ባላስተማረችው ትምህርት መመራት መቀጠሉን በእነዚህና በመሳሰሉት ተጨባጭ ማስረጃዎች መፈተሽ ይቻላል።

ረ) ሃይማኖታዊ ኅብረት ለክርስቲያን ሕይወት ነው

በተለምዶ "ሃይማኖት" የሚለውን ቃል÷ በተለይ በዘመናችን ብዙዎች ለልዩነትና ለመከፋፈል ምክንያት አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያል። እንደ ክርስትና ትምህርት ግን አንድ ሰው በእምነት ሲኖር በሕይወት ይኖራል ማለት ነው።

"... አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።" (ዮሐ.20÷31) ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊትና የክርስቶስ አካል እንደመሆኗ መጠን እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊቀበላቸውና ሊያምንባቸው ከሚገቡት ዋና ዋና ነገሮች መካከል÷ የእግዚአብሔርን አንድነቱንና ሦስትነቱን (አብ÷ወልድ÷መንፈስ ቅዱስ÷ አንድ አምላክ እንደሆነ) የሕያው እግዚአብሔር አንድያ ልጅ ሰውን ለማዳን በግብረ መንፈስ ከድንግል ማርያም እንደተወለደና ፍጹም ሰው እንደሆነ÷ ስለኃጢአታችን በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ÷ እንደሞተና እንደተነሣ÷ በክብር ወደ ሰማይ እንዳረገና በአባቱ ቀኝ እንደ ተቀመጠ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ዳግም እንደሚመጣ ማመን ነው።

በክርስቶስ ደም÷ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ከነገድ÷ ከቋንቋ÷ ከሕዝብና ከወገን የተዋቀረች አንዲት ናት። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ "... በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው..." (ራእ. 5÷9-10)።

ከቃሉ አንጻር ቤተክርስቲያን በዘር÷ በቀለም ሳትወሰን ሁሉን ያቀፈች ሆና ሳለ÷ ብዙዎች በጽንፈኛ አስተሳሰብና ብስለት በጎደለው ልምዳዊ ትምህርት ሥር ስለሚወድቁ የቤተክርስቲያንን ዓላማና ለዓለም የፈሰሰውንም የክርስቶስ ደም በእጅጉ ያደበዝዙታል።

ክርስትና ሕይወት መሆኑ ይቀርና ሃይማኖታዊ ተቋም ይሆንባቸዋል።

ሰ) ሃይማኖታዊ ተቋምን መከተሉ ብቻውን የእምነት ሰው አያሰኝም

የቃሉ እውቀት ይኑረውም አይኑረውም÷ የአንድ ሃይማኖታዊ ተቋም ተከታይ መሆንን ብቻ ትልቅ ትርፍ አድርገው የሚቆጥሩት ብዙዎች ናቸው። በተለይም ከአንዱ የእምነት ድርጅት ወደ ሌላው የፈለሰ ከተገኘማ÷ እንደ ማስታወቂያ ተቆጥሮ በየመድረኩ ቢያቆሙትና ስለ እርሱ ብቻ ቢወራ የማይሰለቻቸው ብዙ መሆናቸውን ከየአቅጣጫው የሚሰማና የታየም ጉዳይ ነው።

የአንድን ሃይማኖታዊ ተቋም አመለካከት በመውረስ ብቻ ደኅንነት የሚገኝ የሚመስላቸው ብዙ ናቸው። በሃይማኖት ሽፋን÷ የገዛ ወገናችንን ስናይ ጥላቻ እየተናነቀን በቃላት መንፈላዊ መምሰልን የተለማመድን ብዙዎች ነን።

የአንድን ሃይማኖታዊ ተቋም ስም በመያዛችንና የዚያ ሃይማኖታዊ ድርጅት ተከታይ በመሆናችን ብቻ ገነት የምንገባ የሚመስለን÷ ገነት የምንገባበትን ትምህርትም ሆነ እምነት ያልተረዳን ብዙዎች እንኖራለን።

በእውቀት እጦት እየጠፉ ያሉት ነፍሳት የሚድኑበትን የሕይወት መንገድ በትሕትናና በፍቅር ማሳየት ሲገባ "መበሻሸቅ" በሚሉት ፈሊጥ አንዱ ሌላውን ለማብሸቅ የሚያደርገውን ዘመቻ ያስተዋለ ክርስቲያን ሁሉ ማዘኑ የማይቀር ነው። አንድ ጊዜ በአንድ ታክሲ እየተጓዝን ሳለ በተጓዦች መካከል የተከሰተው መበሻሸቅ ትዝ ይለኛል።

አንደኛው ተሳታፊ ገና ወንበር ላይ ቁጭ ሲል "በኢየሱስ ስም" ሲል ሌላኛው ደግሞ "በማርያም ስም" አለ። አሁንም አንዱ "ኢየሱስ ያድናል" ሲል ሁለተኛው ደግሞ "ማርያም ታድናለች" አለ። "መዳን በጌታ ነው" ሲል "ያለ ወላዲት አምላክ ዓለም አይድንም" አለ። በሁለቱ መካከል በተፈጠረው የስሜት ንግግር አንዳንዶቹ ሲስቁ፣ አንዳንዶች ደግሞ የሁለቱንም ስሜታዊ ሃይማኖተኝነታቸውን በትዝብት ይመለከቱአቸው ነበር። ከቃሉ እውቀት ይልቅ በሰውኛ አባባል የሚነጉድ÷ ያለቦታው ስለ ክርስቶስ ስም መስካሪና ሐዋርያ መሆን የሚፈልግ በየቦታው ሞልቶአል።

ሸ) "ኢየሱስ ጌታ ነው" "ኢየሱስ ያድናል"

ካለብን ግላዊና ሃይማኖታዊ የስሜት አመለካከት አንጻር ከላይ በሰፈረው ርእስ ብቻ ተመርተን ደግሞ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚል ጥያቄ ውስጥ የምንገባ አንባብያን እንደምንኖር እርግጠኛ ነኝ። ያም ሆነ ይህ የሰፈረው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ ሁሉንም ያስማማል። ከቃሉ ዋና ዓላማ ውጭ አንዳንዶች በስሜትና ቃሉን አዛብተው ሲጠቀሙ ለተመለከተ ደግሞ ሊያበሳጭ ይችላል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነቱም አዳኝነቱም ለሚያምኑቱ ሁሉ እውነት ነው፤ ቃሉም ይህን እውነት ያረጋግጥልናል። "ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር÷ ኢየሱስ የተረገመ የሚል እንደሌለ÷ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፦ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ። (1ቆሮ.12÷3)። "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች

ተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" (የሐዋ.ሥ. 4÷12፤ ማቴ.1÷21)።

ይሁን እንጂ ስለጌትነቱና አዳኝነቱ የሚገልጹትን ኃይለ ቃላት በሆነ ባልሆነ የሚጠሩት ሁሉ የቃሉን አሳብ በትክክል ይገነዘቡታል ወይ? የሚለው አጠያያቂ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ የኢየሱስን አዳኝነት የመሰከረው በክርስቶስ ሰቃዮች (አይሁድ) ሸንጎ ፊት ነበር። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አራትን ስንመለከት÷ ሐዋርያት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ መታዘዛቸውን÷ እነርሱ ግን "ከመናገር ዝም ማለት አንችልም" ሲሉ ስለክርስቶስ ስም የከፈሉትን መሥዋዕትነት እናስተውላለን። (ቁ. 17-20)

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12÷3 ላይ "ኢየሱስ ጌታ ነው" ተብሎ የተገለጸውም ቢሆን ክርስቶስንና ስሙን በሚቃወሙ ነገሥታትና ባለሥልጣናት ፊት ጌትነቱን በመመስከር እስከ ሞት ስለተከፈለውና ስለሚከፈለው ክርስቲያናዊ ምስክርነት የሚያሳይ ነው። አንዳንድ የታሪክ መዛግብት የሚያስረዱን እንጂ÷ በዘመናችን የከበረ ስሙን ቀለል ባለ ልማዳዊ አገላለጽ "ኢየሱስ ጌታ ነው፣ በኢየሱስ ስም÷ ኢየሱስ ያድናል" እንደማለት የተገለጸ አይደለም።

በተለይም የሮማ ቄሳሮች በክርስቲያኖች ላይ ይፈጽሙባቸው የነበረው ስቃይና ግፍ÷ በእነዚህ የመከራ ዘመናትም ቤተ ክርስቲያን ያሳለፈችውን የሰቆቃ ታሪክ ስናስተውል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም መመስከር ምን ዓይነት እንደሆነ እንረዳለን።

የሸዋ ሊቀጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ "የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ" በተሰኘው መጽሐፋቸው÷ የሮማ ነገሥታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሱትን ዕልቂትና ሥቃይ

በመዘርዘር "ቤተ ክርስቲያን እግዚአ ክርስቶስ ነው ስትል የሮማ ቄሣሮች ... የመከራው ዓይነትና ብዛት እየጨመረ ሄደ። እንዲያውም የክርስቲያኖችን ዕልቂትና ሥቃይ የሮማ ቄሣሮች በመዝናኛና በዕረፍት ሰዓታቸው ይመለከቱት ነበር።" ብለዋል (ገጽ 36)። እንዲያም ሆኖ ግን የኢየሱስ ክርስቶስን የጌትነቱን ስም ማንሣትና መመስከርን አላቆሙም ነበር።

"ኢየሱስ ጌታ ነው..." ብሎን መመስከር ለማንና የት መሆኑን ጭምር የምንማርበት ታሪክም ነው የመጀመሪያዪቱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። በእርግጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሁሉ ስለ ስሙ መመስከር አለበት (የሐዋ.ሥ.1÷8)። በሰው ፊት የማይመሰክርለትን ሁሉ እርሱም በሰማያት ባለው አባቱ ፊት ይክደዋል (ማቴ.10÷38)። ነገር ግን ሁሉም በአግባብና በሥርዓት÷ እንደ ቃሉ ሲፈጸም እንጂ አለቦታው ከሆነ "ኢየሱስ ጌታ ነው" የሚለው የከበረውን ዕንቁ በእሪያ ፊት መጣልም ይሆናል። እንዲህ ያለው ሁሉ የክርስትናው እውነትና እውቀት ገብቶት ነው ማለትም አይቻልም።

1.3. የእረኞቻቸው ጥፋት

የእግዚአብሔር ሕዝብ በእውቀት እጦት ለጥፋት የተዳረገበት ዋና ምክንያት መንፈሳዊ ኃላፊነቱን የተቀበሉት ነቢያቱና ካህናቱ የእረኝነት ኃላፊነታቸውን ባመለወጣታቸው ነው። "... በሐሰትም የሚያስተምር ነቢይ እርሱ ጅራት ነው። ይህን ሕዝብ የሚመሩ ያስቱአቸዋል፤ ተመሪዎቹም ይጠፋሉ።" (ኢሳ.9÷15-16)

በሕዝበ እስራኤል ታሪክ ዙሪያ የሚያጠነጥኑት የሕግና የነቢያት መጻሕፍት ሁሉ እንደሚመሰክሩት የሕዝቡ የልብ ጥንካሬ

ብቻ ሳይሆን ታማኝነት የጎደላቸው ነቢያትና ካህናት ለሕዝቡ መጥፋት ተባባሪነታቸው ጎልቶ ይታያል፤ በዚህም ተወቅሠዋል።

ዕውሮች÷እውቀት የጎደላቸው÷ የማያስተውሉ እረኞችና ጥቅመኞች ተብለዋል (ኢሳ. 56÷10-11)። በነቢዩ ሚክያስ በኩል ደግሞ ካህናቱን ነቢያቱንና በአጠቃላይ የሕዝቡን መሪዎች "የሕዝቤን ሥጋ በልታችኋል" በማለት ነቢያቱ ሕዝቡን እንዳሳሳቱት÷ ገዥዎች በጉቦ እንደሚፈርዱ÷ከህናቱም በዋጋ እንደሚያስተምሩ የሕዝቡን ሥቃይ የተመለከተው አምላክ ክፉ ሥራቸው ገልጦአል። (ሚክ. 3÷3፤ 5 እና 11)።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ መጥፋት ደንታ ያልነበራቸውን እረኞችም ወቦሳቸው ብሎአል። ሕዝቤን "ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር። ... በጎቼን በትናችኋል፤ አባርራችኋቸውማል፤ አልጎበኛችኋቸውምም፤" (ኤር.23÷1-2)። በአጭሩ የእረኞቻቸው ችግር ሕዝቡን "የጠፉ በጎች" አስኝቶአቸዋል (ኤር. 50÷6)።

በነቢዩ ሕዝቅኤልም እነዚህ እረኞች ሕዝቡን ለራሳቸው ጥቅም ከመገልገል በቀር÷ የባዘነውንና የጠፋውን ግን እንዳልፈለጉ ተገልጾአል። "በጎቼም በምድር ሁሉ ላይ ተበትነዋል፤የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም።" ይላል (ሕዝ. 34÷2-6)።

ሕዝቡ እንዲጠፋ ምክንያት የሆኑት መንፈሳዊውን መሪነት የያዙት ካህናቱና ነቢያቱ መሆናቸውን ከላይ የተመለከትነው የሕዝበ እስራኤል እረኞች ሁኔታ ያስረዳናል። ለሕዝቡ መጥፋት ምክንያት የሆነውንና ሕጉን ማስተማር÷ማስጠበቅ የነበረበትን ካህንም "እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህን ሕግ ረስተሃልና" መባሉን እንደገና ማስታወስ ይገባናል (ሆሴ. 4÷6)።

ዛሬስ መንፈሳዊ መሪዎች ወይም ካህኑና ሕዝቡ በምን ሁኔታ ላይ ነው የሚገኙት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚገባን ይመስለኛል። መንፈሳዊ እውቀት ከማጣት የተነሣ የዘላለም ሞት መኖሩን መገንዘብ አለብን። ማንም ይሁን ማን ቃሉን ካላወቀ÷ ካልሰማና ካላመነ ይስታል፤ከመዳን ውጪም ይሆናል (ማቴ.22÷29፤ ዮሐ. 5÷24)። መጥፋት ማለትም ቃሉን ሰምቶና አምኖ የዘላለም ሕይወትን አለማግኘት ነው። ሕዝቡ ባለማወቅ ቀንበር ሥር ወድቆ እንዳይጠፋ ካህናቱ ኃላፊነት አለባቸው።

1.4. ቃሉን ማን ያስተምር?

ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን ለማገልገል የተመደቡት ሁሉ የአገልግሎትን ዓላማ እንዲረዱት የማድረግና ሥልጠናም የመስጠት ኃላፊነት አለባት። ይህ ካልሆነ ሕዝቡን ከጥፋት የማዳን ተልዕኮን መወጣት አይቻልም። ካህኑ ባለማስተማሩ÷ ሕዝቡም ባለመማሩ ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ መሆናቸው አይቀርም።

"... የሰው ልጅ ሆይ÷ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው። እኔ ኃጢአተኛውን በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ÷ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል ደሙን ግን በእጅህ እፈልጋለሁ።" (ሕዝ.3÷17-18)።

ይህ መልእክት በተለይም በቤተክርስቲያናችን በእረኝነት ደረጃ ያሉትን ሁሉ ያካትታል። ሕዝበ ክርስቲያኑን ምን ያህል በቃሉ እያስጠነቀቀን ወደ ፈጣሪው የሚመለስበትን ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው? ብለን ራሳችንን መገምገም የባዘኑትን ነፍሳትም ቆም ብሎ የሚመለክት እረኛ መሆንን ይጠይቃል።

1.5. በቤተ ክርስቲያን ያሉ ችግሮች

ቤተ ክርስቲያን ስንል በዋናነት በክርስቶስ ደም የተዋጀውን የእግዚአብሔር መንጋ እያሰብን ነው። ይህ መንጋ ደግሞ ጠባቂ÷ ተንከባካቢ÷ ቃሉንም የሚመግበው ያስፈልገዋል (የሐዋ.ሥ. 20÷28፤ 1ጴጥ.5÷2)።

ይህን የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ሳይገነዘቡት÷ ወይም ምንደኛ በሆነ አስተሳሰብ ተይዘው የስም መንፈሳዊ መሪዎች የሆኑ ብዙ ናቸው። የቤተክርስቲያን ዋና ችግርዋ እየሆነ የመጣውም ይኸው ዓላማን በሳተ ኃላፊነት የሚኖሩ መሪዎች ጉዳይ ነው።

- ዘር÷ ወንዝና ቋንቋ ስንቁጠር ሕዝቡን ለጥፋት የዳረግን አገልጋዮች ብዙዎች ነን፤
- የግል ጥቅማችንን ብቻ ስናሰላ (ስናሳድድ) መንጋውን የበተንን ምንደኞች ብዙዎች ነን፤
- በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኃላፊነት መሥራት ትተን በመሥረቅ÷ በመዝረፍ÷ በሠራተኛው ላይ የበላይነትን በማሳየት (አምባገነን በመሆን)÷በሥነ ምግባር ጉድለትና በመሳሰሉት ቤተ ክርስቲያንን ለአደጋ እንድትጋለጥ በር የከፈትን ብዙዎች ነን።

እንዲያውም በኃላፊነት ላይ ሆኖ አለመስረቅ ሞኝነትና ንቃት የጎደለው አስተሳሰብ ተደርጎ በሚወሰድበት ጊዜ ላይ ነን። እነዚህ ሁሉ የቤተክርስቲያን የረጅም ጊዜ ችግሮቿ ናቸው።

"ከእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ስሜቶቻችሁ አይደሉምን?" እንዲል (ያዕ.4÷1) በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩት አብዛኞቹ ችግሮቻችን ስግብግብነት÷ የግል ምኞትና ራስ ወዳድነት ናቸው።

ሁሉም የራሱን ጥቅምና አጀንዳ ብቻ ይዞ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲገባ ቤተክርስቲያን ትታመሳለች÷ የእርስ በእርስ ውጊያው በዚያው ልክ ይጧጧፋል።

ይህን ያላስተዋለው ምስኪን ሕዝብ ደግሞ አንዱ ለሌላው መሣሪያና ቡድን በመሆን ቤተክርስቲያንን ለከፋ አደጋ እንድትጋለጥ አጋዥ ይሆናል።

❋ መንፈሳዊ ኃላፊነትና የገንዘብ ፍቅር

ገንዘብ÷ ለእያንዳንዱ ሰው የዕለት ተዕለት ሕይወት አስፈላጊ ነው። ለመንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋትና ጠንቅ እንዳይሆን መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑም ተገልጸአል (ማቴ.6÷24፤ ሉቃ.12÷15)። ገንዘብ ወይም ሀብት በራሱ መጥፎ ነው ማለት ግን አይደለም። ይሁን እንጂ ስግብግብነትና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ባለጠጋ ለመሆን መፈለግ ለጥፋት ይዳርጋል።

"ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና÷ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።" (1ጢሞ.6÷9-10)።

እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ዋና ነገር የገንዘብ ፍቅር የሚያስከትላቸውን አደጋዎች ነው።

1. በፈተና ወጥመድ መውደቅ፤
2. ከሃይማኖት መንገድ መውጣት፤ እና
3. ራስን ለሥቃይ መዳረግ ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ ወደ ጥፋት የሚወስዱ መሆናቸውን ልብ ይለዋል።

የገንዘብ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት እንዳለ ሆኖ÷ ተገቢ ያልሆነውን የሀብት ክምችት ጌታ መቃወሙን ቅዱስ ወንጌል ይተርካል። ጌታችን አንድ ሰው÷ ገንዘቡን እንዴት መጠቀም እንዳለበትና በተሰጠው ሀብት ለአምላኩ እንዴት ታማኝ መሆን እንደሚገባው በምሳሌ ሲያስተምር የሰሙት የሃይማኖት መሪዎች ግን አፈዙበት።

"ፈሪሳውያን" የተባሉት የሃይማኖት መሪዎች÷ ከነበረባቸው ፍቅረ ንዋይና ገንዘብን የማከማቸት ተግባር የተነሣ ትምህርቱን ይቃወሙት ነበር። "ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር።" ተብሎአል (ሉቃ.16÷14) "ታሪክ ራሱን ይደግማል" እንዲሉ ዛሬም ቢሆን ገንዘብ በአንድም በሌላ መንገድ የቤተክርስቲያን ጠንቅና÷ የወንጌል እንቅፋት ሆኗል። ተገቢ ያልሆነ የዐመፅ ገንዘብ።

ምዕራፍ ሁለት

2. ጥፋት ምንድነው?

ጥፋት (መጥፋት) የሚለው ቃል ሲሰማ እጅግ ይከብዳል። በቤታችን ውስጥ የተለከሰችው ጧፍ ወይም ሻማ እንኳ በአጋጣሚ ስትጠፋ ለጨለማ አጋልጣን መያዣ መጨበጫ እንደምታሳጣን እናውቃለን። መብራት ሲጠፋ የብርሃን ህልውና ተገፎ ጨለማ ስፍራውን ይቆጣጠራል። ይህ ሲሆን የማይቆጭ÷ የጠፋው መብራት በርቶ መጥቶ ማየትን የማይናፍቅ ሰው ይኖራል ማለት ዘበት ነው።

ሰውን ያህል ክቡር ፍጥረት ሲጠፋ ማየትማ ምን ያህል ይከብዳል! በኖኅ ዘመን የሰው ክፋት ለለበዛ አሳቡና ምኞቱ ሁሉ

ስለከፋ ከኖኅና ከቤተሰቡ በቀር ሌላው የሰው ዘር ዘሙሉ ጠፋ (ዘፍ.6÷5-7)።

ለብርሃንነት የምትታገለግለው ሻማ ከቦታዋ ስትጠፋ ሥፍራው ጨለማ እንደሚሆን ሁሉ የሰው ሕይወትም ብርሃን ከሆነው አምላክዋ ስትለይ ትጠፋለች። "በእርሱ ሕይወት ነበረች ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።" እንዲል (ዮሐ.1÷4)። "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ .. እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤" የሚለው የዳዊት መዝሙርም ይህን እውነት ያስታውሰናል (መዝ.26(27)÷1)።

2.1. የጥፋት ልጅ

ጥፋት በዋናነት ከእግዚአብሔር መለየትንና ከጸጋው መውጣትን ያመለክታል (መዝ.71(72)÷41)። ከሐዋርያት አንዱ የነበረው ይሁዳ "የጥፋት ልጅ" ተብሎአል (ዮሐ. 17÷12)። የወንጌልን እውነት የሚቃወሙና ተገቢ ላልሆነ ብልጥግና የሚስገበገቡ ጥፋት እንደሚገጥማቸው ተጽፎአል (ፊል.1÷28፤ 1ጢሞ.6÷9)። እግዚአብሔርን የሚያውቁትና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙት ሁሉ "በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።" ይላል (2ተሰ. 1÷8-10 ይመልከቱ)።

እምነት የለሽ ስለሆኑትና የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ስለማይቀበሉት ሰዎች "ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም።" ተብሎአል (1ተሰ. 5÷3)።

2.2. እግዚአብሔር የሰውን ጥፋት አይፈልግም

የእኛ የምንላት ንብረታችን ከአጃችን አምልጣ ብትወድቅና ብትጠፋ÷ አሊያም ያስቀመጥነውን ዕቃ ከቦታው ብናጣው ያን ዕቃ እያስታወስን መቆጨታችን አይቀርም።

ሰውን ያህል ክቡርና ውድ ፍጥረት ሲጠፋ ማየት ደግሞ ከምንም በላይ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል። ተቅበዝብዞና ጠፍቶ የነበረውን ሰው ለማዳን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ወደዚህ ዓለም የመጣውም ለዚህ ነው (ኢሳ. 53÷6፣ ሉቃ.19÷10)።

ሰው ጠፍቶ ከሚቀርባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ከኃጢአቱ በንስሐ ወደ ፈጣሪው ከመመለስ ይልቅ አብዝቶ ከእግዚአብሔር የሚርቅና ስለጥፋቱ ግድ የሌለው መሆኑ ነው። ያም ሆኖ ግን የሰውን ጥፋት የማይፈልገው ታጋሽና መሓሪ አምላክ ከጥፋቱ የሚድንበትን ዕድሜ ያበረክትለታል። በመጽሐፍ ቅዱስ፦

"ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።" (2ጴጥ.3÷9) የሚል ቃል እናገኛለን። ብዙ ሰው ግን ይህን የፈጣሪ ትዕግሥት አያስተውልም።

ጌታችን ወደዚህ ዓለም በመጣበት ጊዜ ሕዝቡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ያህል ተጨንቀው÷ ተጥለውና ባዘነው ነበር። ከዚህም የተነሣ ዐዘነላቸው (ማቴ.9÷36)። ደቀመዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲያሰማራቸውም "ወደ ጠፉት በጎች" በማለት ነበር (ማቴ.10÷6)። በመጨረሻም ወደ ጠፋው ዓለምም ሁሉ ልኮአቸዋል (ማር.16÷15)።

2.3. መጥፋት ወይም አለመጥፋት

እግዚአብሔር አምላክ ከጥንት ጀምሮ ሰው ወደ ጥፋት እንዳይሄድ በሕይወትም እንዲኖር በቃሉ አማካይነት ሲያስጠነቅቅና ሲመክር ይታያል (ዘፍ.2÷17)። የእግዚአብሔር ቃል በተለያየ ጊዜ÷ በተለያየ መንገድ ወደ ሰዎች መጥቶአል። ቃሉ ሰዎች በራሳቸው ውሳኔ እንዲጠቀሙበት ከፈጣሪ የተገኘ ነጻ ስጦታ ነው። እንደ ቃሉ ለመኖር ካልፈለጉና ከጣሉት ግን ጥፋት ያገኛቸዋል።

"የመስቀሉ ቃል ሊሚጠፉት ሞኝነት÷ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።" (1ቆሮ.1÷18) እንዳለ ሐዋርያው በመጨረሻው ዘመን ለሚጠፉትና ለሚድኑት ልዩ ምልክት ተደርጎ የቀረበው የመስቀሉ ቃል (ኃጢአተኞችን ለማዳን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ የሚለው ቃል) ነው። እግዚአብሔር አምላካችን ምንም እንኳ ከቀድሞ ጀምሮ የሰው ልጅ ከጥፋት እንዲጠበቅ በቃሉ ሲናገር መቆየቱ ቢታወቅም ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከጥፋት መዳንም ሆነ ወደ ጥፋት መጓዝ የሚረጋገጠው የመስቀሉን ቃል በማመንና ባለማመን ነው።

ይህ ማለት ክርስቶስ ለጠፋው የሰው ልጅ በመስቀል ላይ የከፈለውን መሥዋዕትነትና የፈጸመውን የማዳን ሥራ የሚያስተምረውን ቃለ ወንጌል ማመን ነው። ምክንያቱም የማዳን የምሥራች ቃል በዚህ ወንጌል ተገልጦአልና። (ሉቃ.2÷10-11)። ነገር ግን ብዙዎች ይህን አይቀበሉትም። ወደ ጥፋት የሚወስድ መንገድ መኖሩንና በዚያ የጥፋት መንገድ የሚሄዱት ብዙ መሆናቸውን በቅዱስ ቃሉ ተጽፎ እናገኛለን። "በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ÷ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ

እርሱም የሚገቡ ብዙ ናቸው" ይላል (ማቴ.7÷13)። ቃሉ እያንዳንዱ ሰው መንገዱንና ኑሮውን በማየት በየትኛው መንገድ ላይ መቆሙን እንዲያስተውል ይጋብዛል።

ምዕራፍ ሦስት

3. እግዚአብሔርን እወቅ

በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረው ሰው ፈጣሪውን አለማወቁ ከሁሉም የሚከፋ ኃጢአት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ፈጣሪውን ባለማወቁ ከእንስሳት አንሶ ስለተገኘ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የተናገረውን ቃል ነቢዩ እንደሚከተለው ጽፎታል።

"እግዚአብሔር ተናግሮአልና ሰማያት ስሙ÷ምድርም አድምጪ፤ ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም÷ እነርሱም ዐመፁብኝ። በሬ የገዣውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ፤ እስራኤል ግን አላወቀም÷ ሕዝቤም አላስተዋለም።" (ኢሳ.1÷2-3)።

"ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ እኔም እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ÷ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ÷እኔ እግዚአብሔር ነኝ÷ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም።" (ኢሳ.43÷10-11) ብቸኛ አዳኝ የሆነውን እግዚአብሔር ማወቅ ለሰው ሁሉ ዕረፍትና ሰላም የሚገኝበት መንገድ ነው።

"የእግዚአብሔር ሕዝብ" ተብሎ እግዚአብሔርን አለማወቅ እንዴት አሳዛኝ ነው!! ይህ ደግሞ ዓለማዊ ጠባይ ነው። እግዚአብሔርን የማያውቅ እግዚአብሔርንም የማያሳውቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ የለም። የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት "የአባትህን አምላክ እወቅ" ሲል ሰሎሞንን አዞታል (1ዜና.28÷9)።

እግዚአብሔርን ሳያውቁ እንደፈቃዱም ሳይኖሩ የሚፈጽሙትን ሃይማኖታውያን ሥርዓቶች ሳይቀሩ በእግዚአብሔር ፊት ተነቅአዋል።

3.1. ከመሥዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ

ሰዎች ሃይማኖታዊ ሥርዓትን አስመልክተው ለአምላካቸው የሚያቀርቡአቸው ስጦታዎች መሥዋዕት በሚለው ቃል ሊጠቃለሉ ይችላሉ። "መሥዋዕት" በመጽሐፍ ቅዱስ ሰፊና ዝርዝር ታሪክ ያለው ሲሆን በዚህ ነጥብ ሥር እንድናየው የተፈለገው ግን ከመሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ መቅደም እንደሚገባው ነው።

"ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን÷ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና።" (ሆሴ.6÷6)። "በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ÷ መታዘዝ ከመሥዋዕት÷ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።" (1ሳሙ.15÷22)።

እዚህ ላይ እየተባለ ያለው መሥዋዕት አያስፈልግም ሳይሆን÷ በቅድሚያ የምንሠዋለትን አምላክ ማወቅና ለእርሱ ያስፈልጋል ነው። መሥዋዕት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለውም እግዚአብሔርን አውቀን ለቃሉም ታዘን ስናቀርበውና ባልጀራችንን መውደድና ምሕረት (ይቅርታ) ማድረግ ለሚገባን ሰዎች ምሕረት ስናደርግላቸው ብቻ ነው (ኢሳ.1÷11-17፤ አሞ. 5÷21-22፤ ማቴ. 12÷7)።

3.2. እውቀት የጎደለበት የዮፍታሔ መሥዋዕት

ከመሳፍንተ እስራኤል አንዱ የሆነው ዮፍታሔ አሞናውያንን በታላቅ እግዚአብሔርና በእምነት ድል ቢያደርጋቸውም የቃሉ አጠቃቀት ጎድሎት ነበርና የሚወዳት አንዲት ሴት ልጁን ተገቢ ባልሆነ ሥእለት መሥዋዕት አድርጎ ሠውቷታል (መሳ. 11÷29-39)።

እንዲህ ዓይነቱ መሥዋዕት አሕዛባዊ መሥዋዕት ነው። እነርሱ ልጆቻቸውን በእሳት ያሳልፉ ነበር። እግዚአብሔር ደግሞ ሕዝቡን ከእንዲህ ዓይነቱ አሕዛባዊ መሥዋዕት እንዲጠበቁ በሙሴ በኩል አስቀድሞ አዞአቸዋል። "እንዲሁ ደግሞ እኔ አደርጋለሁ ብለህ ስለ አማልክቶቻቸው እንዳትጠይቅ ተጠንቀቅ።" ብሎታል (ዘዳ. 12÷29-31)። ዮፍታሔ ግን አስቀድሞ የተጻፈውን ሕግ አላስተዋለም ነበርና በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሰላም የሚነሣውን ተገቢ ያልሆነ ድርጊት በመፈጸም (ልጁን በመሠዋት) ስሕተት ሠራ።

"መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።" (ማቴ.22÷29) እንደተባለው ምንም ያህል ሃይማኖታዊ መልክ ቢኖራቸው የመጻሕፍትን እውነት ያልተከተሉ ሰዎች ተግባር የተሳሳተ ነው። በዘመናችንም ሃይማኖታውያን ሥርዓቶችን ለመፈጸም ብቻ የሚሮጡ÷ቃሉ ምን እንደሚል ግን ማወቅ የማይፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። እግዚአብሔርም በቃሉ መሠረት ካላወቅነው እንጠፋለንና የእግዚአብሔርን ቃል እንወቅ። በቃሉም አማካይነት እግዚአብሔርን እናውቃለን።

3.3. የድፍረት መሥዋዕት

መሥዋዕት ባለማስተዋል ብቻ ሳይሆን በድፍረት የሚቀርብበት ጊዜ አለ። የአምላካቸውን ፈቃድ ሳይፈጽሙ በለመዱት ሥርዓታቸው ብቻ በድፍረት መሥዋዕት ያቀርቡ የነበሩት እስራኤላውያን እንዲህ በምጸታዊ ቃል ተወቅሠዋል።

"የእስራኤል ልጆች ሆይ÷ ይህን ወድዳችኋልና ወደ ቤቴል ኑና ኃጢአት ሥሩ፤ ወደ ገልገላ ኑና ኃጢአትን አብዙ፤ በየማለዳውም መሥዋዕታችሁን÷ በሦስተኛውም ቀን አሥራታችሁን አቅርቡ፤ እርሾ ካለበትም የምስጋናውን መሥዋዕት አቅርቡ÷ በፈቃዳችሁም የምታቀርቡትን አውጁ አውሩ÷ ይላልና ጌታ እግዚአብሔር።" (አሞ.4÷4-5)።

ድፍረት የሚመጣው እግዚአብሔርን በፍርሀትና በተገቢ መንገድ ያለማወቅና ያለመታዘዝ ነገር በሕይወታችን ሲሠለጥን ነው። በእግዚአብሔር የማደሪያው ድንኳን÷ መሥዋዕተ አሪት በሚሠዋበትና ታቦቱ ባለበት ይኖሩ የነበሩት የሊቀ ካህናቱ የዔሊ ልጆች (አፍኒንና ፊንሐስ) እግዚአብሔርን ባለማወቅ በፈጸሙት ድፍረት ተቀጥተዋል።

የእግዚአብሔር ቃል ማንነታቸውን ሲገልጥ "ምናምንቴዎችና እግዚአብሔርንም አያውቁም ነበር።" ይላል (1ሳሙ.2÷12)። እግዚአብሔርን አለማወቅ ማለት ከእርሱ ጋር በግል ሕይወታችን ኅብረት አለማድረግ ወይም እርሱን አለመፍራት ማለት ነው። የእነዚህን ሰዎች ትዕቢትና በእግዚአብሔር ፊት የፈጸሙትን የኃጢአት ዓይነት በቁጥር 16 እና 22 ላይ መመልከት ይቻላል።

3.4. እግዚአብሔርን የማወቅ ፍላጎታችንን እርሱ ያውቀዋል

"የእግዚአብሔር ሕዝብ ነኝ" ለሚል ሰው እግዚአብሔርን የማወቅ ጉዳይ በጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነገር አይደለም። እርሱን ለማወቅ ያለንን ጉጉት (ፍላጎት) ደግሞ ከማንም በላይ እርሱ ያውቀዋል። "እናንተ ትሹኛላችሁ÷ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ። ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ÷ይላል እግዚአብሔር" (ኤር.29÷13-14)።

"አውቅህ ዘንድ በፊትህም ሞገስን አገኝ ዘንድ መንገድህን ስላወቅሁህ ይህን ያልኸውን ነገር አደርጋለሁ" ብሎታል እባክህ አሳየኝ" ሲል ለጠየቀው ሙሴ (ዘጸ.33÷13፤17)። እግዚአብሔርን አውቆ በፊቱም በሞገስና በክብር ከመታወቅ የሚበልጥ ምን ነገር ይኖራል! "እግዚአብሔርን ማወቅ" ስንል "መከተል" "በፊቱም በሕይወት መኖር ነው" (ሆሴ. 6÷2-3)። መሻታችን በትክክል እግዚአብሔርን ማወቅ ከሆነ እርሱን የምናውቅበትን ልብ የሚሰጠን ራሱ እንጂ ማንም አይደለም (ኤር.24÷7፣ ዘካ.2÷11)።

እግዚአብሔር÷ በእግዚአብሔርነቱ ብቻ ሊታወቅ ሊመሰገንም ይገባዋል። እግዚአብሔርን አለማወቅ÷አሳቡንም አለማስተዋል አሕዛብነት ነው (ሚክ. 4÷12)። እግዚአብሔርን በአምላክነቱ የሚያውቅ ሕዝብ ለዘላለም አያፍርም (ሚክ.2÷27፣ ጢሞ.1÷12)። እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ የሚፈልግ ሰው ያገኘዋል

(ኤር.29÷13)። እግዚአብሔርን የማይፈልግ÷ የማያስላም ይጠፋል (ሶፎ.1÷6)።

✸ የእግዚአብሔር ፍቅር ለሕዝቡ

አምላካቸውን ካለማወቃቸው የተነሣ ወደ ጥፋት እየነጎዱ የነበሩትን ሕዝበ እሥራኤል የእግዚአብሔር ፍቅር እየተከተላቸው መሆኑን ከነቢዩ ሆሴዕ የትንቢት መጽሐፍ እናነባለን። "አብዝቼ ብጠራቸው አጥብቀው ከፊቴ ራቁ፤ ... እኔ እፈውሳቸው እንደነበርሁ አላወቁም። በሰው ገመድ በፍቅርም እሥራት ሳብኋቸው፤ ..." (ሆሴ.11÷1-4)። እግዚአብሔር እንደ ሰው አይደለም፤ አምላክነቱንና ፍቅሩን ማወቅ የተሳናቸው ሕዝቦች ከፊቱ እየሸሹ÷ እርሱ ግን ወረት በሌለው አባታዊ ፍቅሩ እየተከተላቸው ይጠራቸዋል።

ዛሬም ቢሆን የብዙ ሰው ጠባይ ይኸው ነው። እግዚአብሔር በዕድሜ ዘመናቸው ሁሉ በፍቅር እየተከተላቸው ሊያውቁትና ሊከተሉት÷ ሊያስተውሉትም ሲገባቸው እርሱን አለመፈለግና ደንታ ቢስ መሆን ይታይባቸዋል። ያም ሆኖ እግዚአብሔር ግን ዐመፀኛውን ሰው በፍቅሩ ወደ ራሱ ለመሰብሰብ ዛሬ በፍቅር ቃሉ ይጠራቸዋል። ለዚህም ነው "ወደ ዐመፀኛ ሕዝብ ቀኑን ሁሉ እጆቼን ዘረጋሁ።" የሚለው (ኢሳ.65÷2)። በእውነት የእግዚአብሔርን ፍቅር በትክክል ያወቀ ሰው አዋቂ ነው።

3.5. እግዚአብሔርን አለማወቅ ሕይወት

እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ ማለት የሚቻለው አእምሮአዊ በሆነ እውቀት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር እንደ ፈቃዱ የሆነ መንፈሳዊ ኅብረት መመሥረት ሲቻል ነው። አውቀዋለሁ የሚሉ

ነገር ግን ያላወቁት ነበሩ። ከእነዚህም መካከል አንዱ ሳውል (ሐዋርያው ጳውሎስ) ነው። ራሱን ጻድቅና የእግዚአብሔር ሰው በማድረግ÷ አጉል በሆነ ቅናት ተይዞ ቤተክርስቲያንን ያሰልክ ሲያሳደድ የነበረ÷ የማያውቅ አዋቂ ነበር (ፊል.3÷5-6)።

እግዚአብሔርን አውቀውት እንደ ፈቃዱ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ለማሳሰርና ለመግደል ጉዞ ላይ እያለ በመሣት እያለ በድንገት ከሰማይ የሚያንጸባርቅ ብርሃን በራለት። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ታሪኩን በሰፊው እንደምናገኘው÷ ባለማወቅ ሕይወት ተይዞ አሳዳጅ የነበረው ሳውል÷ አምላኩን ካወቀ በኋላ ለአምላኩ ፈቃድ ብቻ የሚኖር ሆነ።

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔርን በቃሉ መሠረት ያላወቀ ሰው ሕይወቱ አስቸጋሪ መሆኑ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሰማያዊ ብርሃን ያልበራለት ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ምንጊዜም እንደሚቸገር የጳውሎስ ሕይወት በቂ ትምህርት ይሰጣል።

ጻፎችና ፈሪሳውያን የሚባሉት አስቸጋሪ የሃይማኖት ሰዎች እግዚአብሔርን እናውቃለን ብለው የሚኩራሩ ነበሩ። ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ግን ማመንም ሆነ ማወቅ አልፈለጉም። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመልስላቸው፦ "እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር" ብሎአቸዋል (ዮሐ.8÷19)። ለአዲስ ኪዳን አማኞች እግዚአብሔር ማንነቱን የገለጠው በልጁ በኩል ነውና ልጁን የማያውቅ ሁለ3ኤባቱን አያውቅም በአጠቃላይም እግዚአብሔርን አያውቅም።

ሀ) እግዚአብሔርን ያወቀ ሰው ለእግዚአብሔር ክብር ይኖራል

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት ...." እንደተባለው እግዚአብሔርን ዐውቆ የዘላለም ሕይወት ያገኘ ሰው የሚኖረው ለእግዚአብሔር ክብር ነው (ዮሐ.17÷3)። ሐዋርያው ጳውሎስ አምላኩን ካወቀ በኋላ ሕይወቱን እስከ መስጠት ድረስ ለአምላኩ ክብር ኖሯል።

ክርስቶስን ካወቀ በኋላ ያለውን ሕይወቱን ሲመለከት ያላለፈው ዘመኑ ሁሉ ጉድፍና ውርደት የሞላበት አሳፋሪ ሕይወት እንደነበረ አስተዋለ (ፊል.3÷8-9 ይመልከቱ)። "አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና" ሲል (2ጢሞ.1÷12) በሚያሳፍር ያለማወቅ ሕይወት የነበረበትን ሁኔታ አስታወሰ። ክርስቶስን በትክክል ያወቀ ሰው "እግዚአብሔር" የሚለውን በትክክል ያውቃል፤ ለእርሱ ክብርም መኖር ይጀምራል። እንዲያውም እግዚአብሔርን ማወቅ የሚለካው በምንኖረው ክርስቲያናዊ ኑሮ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (1ዮሐ.2÷3-6)።

ለ) ለመግደልም ጸም?

ጳውሎስ ለአምላኩ ክብር መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ስደት በዝቶበታል። በእግዚአብሔር ፊት በመልካም ኅሊና መኖርም የጳውሎስ ቋሚ ተግባሩ ሆነ (የሐዋ.ሥራ.23÷1)።

ነገር ግን ሃይማኖተኞች ነን ከሚሉት የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ጋር ግንባር የፈጠሩ ከአርባ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሐዋርያው [illegible] እስኪገደል ያረፉ ምንም አለመቅመስ" ተማማሉ

(ቁ.12-14)። እግዚአብሔርን ማወቅ የሌለበት ሃይማኖተኛነት ከሁሉም የከፋ ነው ያልኩት ለዚህ ነው።

በጸም በጸሎቱ የሚታወቅ "ዳዊት ሳይደግም እህል በአፉ ውስጥ አያስገባም" ተብሎ የሚነገርለት አንድ ሽፍታ ነበረ ይባላል። ከጋሻ ጃግሬዎቹ ጋር በጫካ ውስጥ በመሆን የሚዘርፉትን አሳፊ አግዳሚ እየተጠባበቁ ሳለ አንድ ነጋዴ ይመጣል። "ጸሎተኛው" ሽፍታ ዳዊት እየደገመ ስለሆነ አሽከሮቹ ንብረቱን ሊቀሙት ቢታገሉም አልሆንላቸው ይላል። በዚህ ጊዜ ከአሽከሮቹ አንዱ ወደ ሽፍታው ቀረብ በማለት በምልክት የሰውየውን እንቢተኛነት ቢነግረው÷ ጸሎቱን ላለማቋረጥ ሲል ብቻ እርሱም በምልክት "አንገቱን ቁረጡትና ግደሉት" አለ ይባላል። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሃይማኖተኛ መሰል ሰዎች የሚፈጽሙአቸውን የክፋት ድርጊቶች ሲመለከቱ ምን ይሰማዎ ይሆን?

ሐ) እየገደሉ እግዚአብሔርን ያገለገሉ መምሰል

የእግዚአብሔርን ሰዎች እያሳደዱ÷ እየገደሉም÷ ጥሩ የሃይማኖት ሰዎች÷ ለእግዚአብሔርና ለአምልኩቱም ቀናእያን የሚመስሉ በየዘመናቱ ተነሥተዋል። ሕይወታቸው ሲፈተሽ ግን እግዚአብሔርን "እናውቀዋለን" የሚሉ÷ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን የማያውቁት ነበሩ።

"እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከምኩራባቸው ያስወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል። ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ ነው። ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ።" (ዮሐ.16÷1-4)

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠውን እግዚአብሔርን ያላወቁ ሁሉ በአንድም በሌላም መንገድ የእግዚአብሔርን እውነት ይቃወማሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ ስሜ ያደርጉባችኋል።" ብሎአል (ዮሐ.15÷21)

ሐ/ጳውሎስ "ብርሃና ለቤተክርስቲያን - የቤተ ክርስቲያን ብርሃኗ" ከመባሉና እግዚአብሔርን በተገቢው መንገድ ከማወቁ በፊት ማሳደድና መገደልን እንደ ትልቅ የሃይማኖት እውቀት የሚቆጥር ሰው ነበር (የሐዋ.ሥራ. 22÷4-5)። ከዚህ ታሪክ÷ እግዚአብሔርን ሳያውቁት ለሃይማኖት መቅናት ወደ ወንጀለኛነት እንደሚመራ እንረዳለን።

የሐዋርያው ጳውሎስ የኑዛዜ ቃል ይህን ሐቅ ያሳየናል። "በአይሁድ ሥርዓት በፊት እንዴት እንደኖርሁ ሰምታችኋልና፤ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ያለልክ አሳድድና አጠፋ ነበር÷ ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር።" ይላል (ገላ.1÷13-14)።

ዛሬም ሃይማኖታዊ ቅናት ብቻ የሚያንገበግበን የእግዚአብሔር ዓላማና እውነተኛ ክርስትና ምን እንደሆነ በውል ያልተረዳን ብዙዎች እንኖራለንና÷ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማወቅና በዘመኑ ፍጻሜ በአንድያ ልጁ በኩል ለዓለም ሁሉ የተገለጠውን ዘላለማዊ እቅድ ማስተዋል ካልቻልን የጎደለብን ዋና መንፈሳዊ እውቀት እንዳለ እናስተውል።

3.6 እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም የነበረ÷ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ዘላለማዊ አምላክ ነው። ሁላችን የእጁ ሥራዎች ነን (መዝ. 99(100)÷3)።

ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር በመናገር ማንነቱን ያውጃል (መዝ.18(19)÷1-2፤ 148)÷3-5)፤ ሮሜ1÷20-23 ይመልከቱ)። ከምንም በላይ እግዚአብሔርን በመጽሐፍ ቅዱስ ማወቅ ይቻላል (ዘፍ.1÷1)። ይልቁንም የማይታየው እግዚአብሔር "የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ" በሆነው በአንድ ልጁ በኩል ታውቆአል፤ ላላወቁት ዛሬም ይታወቃል (ዕብ.1÷1-3፤ 1ዮሐ.1÷1-2፤ ዮሐ.8÷19)።

ምዕራፍ አራት

4. እግዚአብሔር ካህናቱን ገሠጸ

የእግዚአብሔር ሕዝብ በእውቀት ዕጦት መጥፋቱን በትንቢት ሆሴዕ ላይ ተመልክተናል። ይህ ሊሆን የቻለው ግን ካህናቱ የእግዚአብሔርን ሕግ ለሕዝቡ ባለማስተማራቸው ነበር። እግዚአብሔር÷ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህን ሕግ ረስተሃልና" (ሆሴ.4÷6) ሲል ተናገረ። ሕዝቡን ማስተማር የነበረባቸው ካህናት ከሕዝቡ በምንም ተሻለው አልተገኙም። "የሕዝቤ ኃጢአት መብል ሆኖላቸዋል ... እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ" ይላል (ቁ .8-9)። የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆኑት ካህናት በታማኝነት ሕዝቡን ካለማስተማራቸው

የተነሣ "እኔ ደግሞ በሕዝቡ ሁሉ ፊት የተናቃችሁና የተዋረዳችሁ እድርጌአችኋለሁ።" ሲል እግዚአብሔር እንደገና በነቢዩ ሚልኪያስ በኩል ካህናቱን እንዴት እንደ ገሠጻቸው እናያለን (ሚል. 2÷7-9)።

እግዚአብሔር በትእዛዙ የሚሄዱትን ያከብራል፤ ከትእዛዙ ውጪ የሚኖሩትን ደግሞ ይንቃል፤ ያዋርዳልም (1ሳሙ.15÷23)። በተለይም ለአንድ መንፈሳዊ ኃላፊነት የተጠራ አገልጋይ በእግዚአብሔር ፊት ተጠልቶ፤ ተንቆና ተዋርዶ ማየት ከምንም በላይ አሳዛኝ ነው።

● ካህናቱን ስለሕጉ ጠይቅ ተብሎአል

"ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ" እንዲሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማወቅ የሚገባውን እንዲያውቅ ካህናቱ ሕጉን በትክክል እንዲያስተምሩ ታዘዋል። "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ካህናቱን ስለ ሕጉ ጠይቅ" (ሐጌ 2÷11)።

"የእግዚአብሔር ሕግ" ፍጹምና ቅዱስ እንደ መሆኑ (መዝ. 18(19)÷7-8፤ ሮሜ 7÷12) የካህናቱ ድርሻ ይህን ቅዱስ ቃል ለሕዝቡ ማሳወቅ ነበር። ነገር ግን ከህነታዊ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ተወቅሠዋል።

ለአምላካቸው መስጠት የሚገባቸውን ክብርም ትተዋልና "እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ÷ ልጅ አባቱን÷ ባሪያም ጌታውን ያከብራል፤ እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ?" በማለት ገሥጾአቸዋል (ሚል.1÷6)።

ካህናቱ ለእግዚአብሔርና ለሕጉ ግዴለሽ እየሆኑ በመምጣታቸው ለሕዝቡም ደንታ ቢሶች ሆነዋል÷ ሥርዓተ አምልኮውን እንደዚሁ "አስነቀፋችሁት" ተብለዋል (ቁ.7-12

ይመልከቱ)። ሕዝቡን ለጥፋት የዳረጉትም ራሳቸው ከእውነት ጎዳና ፈቀቅ ስላሉ ነው።

4.1. የካህናቱ ታሪክ

በብሉይ ኪዳን የካህናት ተግባር በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በመሆን ሰውንና እግዚአብሔርን ማገናኘት ሲሆን÷ ክህነት "ተክህነ አገለገለ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘና መገልገልን ሳይሆን ማገልገልን የሚያሳይ ቃል ነው። እንደ መልከ ጼዴቅ÷ እንደ አሮን እንደ ዘካርያስና የመሳሰሉ የእግዚአብሔር አገልጋይ ካህናትና ሊቃነ ካህናት የመኖራቸውን ያህል ካህናተ ጣዖታት የሚባሉም አሉ (ሶፎ. 1÷4)። በብሉይም ሆነ በሐዲስ ዘመን ብዙ ዓይነት ካህናት እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይተርካል።

- ርኅራኄ የሌላቸው ካህናት ነበሩ (ሉቃ.10÷31)፤
- ከዐመፅ ጋር የሚያብሩ ካህናት ነበሩ (ማቴ. 27÷20)፤ ለኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀልና መሞት ዋናዎቹ አቀንቃኖች ካህናት ነበሩ (ማቴ. 26÷3-5) ፤ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ቡድን መሪዎችን ጨምሮ ካህናቱ÷ ሕዝቡን በማነሣሣትና በማባበል የክርስቶስን ሞት እውን ለማድረግ ከፍተኛውን ሥራ ሠርተዋል። አብዛኛው የጥፋት ሥራ በእነዚህ ካህናት ቅንብር መከናወኑን ስናይ "... አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ" የሚለውን መለኮታዊ ቃል እንደገና እንድናስታውስና ካህናት ክህነታቸውን በተገቢው መንገድ ካልተጠቀሙበት በእግዚአብሔር ፊት የሚጠሉ መሆኑን ለአዲስ ኪዳን ካህናትም (አገልጋዮች) የሚያስተምረው ዓቢይ መልእክት አለው።

4.2. "ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነው"

ረጅሙን የብሉይ ኪዳን ታሪክ ስንመለከት የክህነት አገልግሎቱ÷ ደካማ ነበረ። ሕጉም ሆነ መሥዋዕቱ ፍጹምነት የጎደለው ስለነበረ ፍጹም ድኅነት አልተገኘበትም። በአዲስ ኪዳን ግን አዲስ የክህነትና የመሥዋዕት ሕግ ተመስርቶአል ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እንደ ገለጸው፦

"እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልናል በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን÷ እንደ አሮን ሹመት የማይቈጠር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደ ፊት ስለ ምን ያስፈልጋል? ክህነቱ ሲለወጥ÷ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና።" ይላል (ዕብ. 7÷11-12)።

የብሉይ ኪዳን ክህነት ከነገደ ሌዊ በመወለድ የተገኘ ሲሆን የአዲስ ኪዳን ክህነት ግን ከነገደ ይሁዳ ሆኖአል፤ ይኸውም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ነው። "እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል" (ዕብ.7÷26) ተብሎ እንደ ተጻፈ ደካማ እንደሆነውና ፍጹምነት እንደጎደለው የብሉይ ኪዳን ክህነት ሳይሆን እንደ መልከጼዴቅ ክህነት የሆነ ፍጹም ክህነት የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ሆኗል (ዕብ. 7÷11-28 ያለውን ይመልከቱ)።

4.3. ክህነት እንደ ቀላል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደካማ የሆነውንና ፍጹምነት የጎደለውን ደካማና ፍፁምነት የጎደለውን የብሉይ ኪዳን ክህነት÷ ፍጹምነት ባለውና ዘላለማዊ በሆነው የራሱ ሊቀ ካህናትነት መተካቱን ከዕብራውያን መልእክት በሰፊው እንማራለን። ሊቀ ካህናት ኢየሱስ

ክርስቶስ "ራሱን" መሥዋዕት በማድረግ ነው የተሻለውን ክህነት የመሠረተው።

የአዲስ ኪዳን አገልግሎት የእምነታችን ራስና ፈጻሚ የሆነውንና በመስቀል ታግሦ በክብር ከፍያለውን ኢየሱስን እየተመለከትን ማገልገል እንጂ (ዕብ. 12÷2) እንደ ልማድ ቆጥረን እንደ ቀላልም አይተን ማለፍ የለብንም። ጌታችን "መልካም እረኛ" ነውና (ዮሐ.10÷10) የአዲስ ኪዳን ካህናትም ከእርሱ የተቀበሉትን መልካም እረኝነት በታማኝነት የሚወጡ መሆን አለባቸው (ኤፌ. 4÷11-13 ይመልከቱ)።

4.4. ካህንና ዲያቆን የመሆን ናፍቆት

"ክህነት" ልዩ የሆነና የከበረ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው። በተለይም ክህነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ገብቶአቸው የሚያገለግሉ መንጋውንም በአግባቡ የሚጠብቁ የክብር አክሊል አላቸው (1ጴጥ. 5÷2-4)። ነገር ግን "ክህነት" ወይም ቅስናና ዲቁና ወዘተ. የከበረ አገልግሎት ቢሆንም በአብዛኞቹ ዘንድ እንደ ልማድና ጊዜያዊ መጠቀሚያ ተደርጎ ስለሚወሰድ ክርስቲያናዊ ዓላማውን ስቶ የሚታይበት ሁኔታ አለ። ብዙዎች ዲያቆንና ቄስ የመሆን ናፍቆታቸው የላቀ ነው፤ ኃላፊነትን በእግዚአብሔር እይታ በመወጣት ረገድ ግን ብዙ የሚቀር ነገር አለ። ይህ ደግሞ ሕዝቡ በእውቀት ዕጦት እንዲጠፋና፤ ቤተ ክርስቲያንም እንድትነቀፍ በር ከፋች ነው።

በቤተክርስቲያናችን ለዲቁናና ለቅስና የሚያበቁት መስፈርቶች በአብዛኛው ከውዳሴ ማርያም እስከ ግብረ ዲቁና፤ ከኪዳን እስከ ቅዳሴ፤ በአጠቃላይም በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓተ አምልኮት ዙሪያ የሚያተኩሩ ናቸው። ለነቢያትና ለሐዋርያት የተሰጠውን የእረኝነት

ተግባርና እንደ ቃለ ወንጌል ሕዝቡን ለመምራት ብዙ የሚቀር ነገር አለ። በቅዱስ ያሬድና በሌሎች የቤተክርስቲያን አባቶች የተደረሰውን ቃለ እግዚአብሔርም ቢሆን ዘሩንና ዜማውን ማጥናት እንጂ የቃሉን ዋና መልእክት በመረዳትና በማስተዋል እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በማምለክ ረገድ መንፈሳዊ ግንዛቤው ብዙም የለም።

በዘመናችን ያለውን የስሕተት እንቅስቃሴ በቃለ ወንጌል መመከት የሚችሉ ምእመኑንም በቤቱ (በቤተክርስቲያን) ጸንቶ እንዲቆም የሚያስችለውን የእውነት ቃል ለመመገብ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ በቂ ግንዛቤ ያላቸው ካህናት (ቀሳውስትና ዲያቆናት) በቤተክርቲያኒቱ እየበዙ ካልሄዱ÷ ወደድንም ጠላንም የቤተክርስቲያናችን ህልውና ፈታኝ ተግዳሮቶች ያጋጥሟታል። ዘመኑ አንድ ጊዜ ቄስ ወይም ዲያቆን ሆኜአለሁ በሚል ብቻ መንፈሳዊ አገልግሎትን ቀለል አድርገን የምናይበት ወይም በምንደኛ አስተሳሰብ ተይዘን አክብሮ በያዘን ሕዝብ ላይ የምንዘባነንበት ጊዜ አይደለም።

ቅስና ወይም ዲቁና ማለት በቤተ መቅደስ ውስጥ ገብቶ መውጣት÷ ብልጭልጭ ልብሶችን ለብሶና ደምቆ መታየት ብቻ የሚመስላቸው በአእምሮ ሕፃናት የሆኑ÷ለትልቁ መንፈሳዊ ኃላፊነት ግንዛቤውም ብስለቱም የሚጎድላቸው ብዙ ናቸው። እነዚህ ሁሉ የቅስናን እና የዲቁናን ምንነት እንዲረዱ በቂ ሥልጠናና ትምህርት ካልተሰጣቸው የቤተ ክርስቲያናችን ቀጣይ ሕይወት አደጋ ላይ መሆኑን በቅን ልቦና ልናስበው ይገባል።

የጸመ ፍልሰታ ሱባኤ ይዘው ሰዓታቱን ሲቆሙ፤ ቅዳሴውን ሲቀድሱ፤ ድንግል ማርያም ከነልጅዋ በገሃድ መጥታ የምታናግራቸው የሚመስላቸው፤ ሱባኤው ሲያበቃ ግን ሁሉን

ትተው ወደ ቀደመው ግብራቸው የሚመለሱ÷ ዓመቱን ጠብቀው የተለመደውን ሱባኤ እስኪይዙ ድረስ በዓለማዊ ጠባይ፣ በዓለማዊ ኑሮ ሕይወታቸውን የሚገፉ ብዙዎች ናቸው።

እግዚአብሔር የሚገኘው በቤተመቅደሱ ውስጥ ብቻ የሚመስላቸው÷ እግዚአብሔርን በአፈ ታሪክ እንጂ በሕይወት ማወቅም ሆነ ከእርሱ ጋር እንዴት በመንፈስ መኖር እንደሚቻል መንፈሳዊ ገንዘቤ የጎደላቸው መኖራቸውን አንክድም። ታዲያ እግዚአብሔርን ለሌላው ለማሳወቅ የእግዚአብሔርን አገልግሎት የተረክብን ካህናትና ዲያቆናት የክህነትን ምስጢር እንደሚገባ ካልተገነዘብነው ሕዝቡን ከጥፋት ማዳን እንዴት እንችላለን? በየዕለቱ በልማድ "በሠራሁት ኃጢአቴ ይፍቱኝ" እያለ ለሚቃትተው ሕዝባችን "እግዚአብሔር ይፍታህ፣ ይፍታሽ" በምትለው የተለመደች ቃል ብቻ ኃላፊነታችንን የተወጣን ይመስለን ይሆን? ወይስ ሕዝቡም እኛም በአምልኮቱ ስፍራ በቤተ መቅደሱ (ቤተክርስቲያን) መገኘታችን ብቻ በቂ መስሎን ይሆን? ይህን ስል በቤተ መቅደሱ ተገኝተን አምልኮታችንን መፈጸማችንን እየነቀፍኩ አይደለም፤ ከአምላካችን ጋር ያለንን ግንኙነት ዓመታዊ ብቻ እንዳናደርገውና የክት ልብስ ይመስል ዓመታዊ በዓላትን ብቻ የምንጠብቅ÷ በሌላው ጊዜ ግን እግዚአብሔር እንደሌለ ቆጥረን ዓመቱን እያሰብን ብቻ መንፈሳውያንና ሱባኤ ገቢዎች እንዳንመስል ለማስገንዘብ ያህል ነው።

ከእግዚአብሔር ፊት በመንፈስ ርቀው (ሸሽተው) ስቤተ መቅደሱ አገልግሎትና ለሥርዓተ አምልኮት ብቻ ሲመላለሱ ለነበሩት ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርሚያስ በኩል እንዲህ ተናግሮአቸዋል።

"እግዚአብሔርን ልታመልኩ በእነዚህ በሮች የምትገቡ ከይሁዳ ያላችሁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ በዚህም ስፍራ አሳድራችኋለሁ። የእግዚአብሔር መቅደስ÷ የእግዚአብሔር መቅደስ÷ የእግዚአብሔር መቅደስ÷ ይህ ነው እያላችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ።" (ኤር. 7÷2-4)። የአብርሃም ዘር በመሆናቸው ብቻ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ ሲመጻደቁ ለነበሩት አይሁዳውያን የተነገራቸውም "ንግግሬን የማታስተውሉ ለምንድን ነው? ቃሌንም ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው። እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሎስ ናችሁ" የሚል ነው (ዮሐ. 8÷43-44) ። ስለዚህ እንደሚገባ ካልሠሩበት ካህን (ቄስ ወይም ዲያቆን) ተብሎ መጠራት ብቻ ከጥፋት አያድንም። እንዲያውም በብዙ ያስጠይቃል።

4.5. የቅስናና የዲቁና መንፈሳውያን መስፈርቶች

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደስ ስላለንና ስለፈለግነው ብቻ የምናገለግለው ሳይሆን ጥሪን ተከትሎና መንፈሳውያን መስፈርቶችን አሟልቶ ማግልገልን የሚጠይቅ ነው። አንድ አገልጋይ ለዚህ መንፈሳዊ ኃላፊነት ሲታጭ ወይም ኃላፊነቱን ሲቀበል÷ ምንም እንኳን የኃላፊነቱ ተዋረድ ቢለያይም÷ ምዕመናንን (ቤተ ክርስቲያንን) ለማገልገል የመሪነት ስፍራ እየተሰጠው መሆኑን ሊያውቅ ይገባል።

በዚህ የቤተ ክርስቲያን የመሪነት አገልግሎት ጳጳስ፣ኤጲስ ቆጶስ (ቄስ) እና ዲያቆን ተብለው በደረጃ የተቀመጡት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቁልፍ ኃላፊነት ሲኖራቸው ብቃታቸውና

መመዘኛ መስፈርታቸውም በቅዱስ መጽሐፍ እንደሚከተለው ሰፍሮአል።

በእርግጥ እነዚህን መስፈርቶች ‹‹የነፍስ አባትና የነፍስ ልጅ የመሆን ምስጢር›› (ክፍል ሁለት) መጽሐፌ ላይ የገለጽኩአቸው ቢሆንም÷ በአጭሩም ቢሆን እንደገና ለመግለጽ እሞክራለሁ። ምክንያቱም እነዚህ መንፈሳውያን መስፈርቶች የሌሉባት ቤተ ክርስቲያን ሊወድቅ እንደ ዘመመ ቤት አደጋ የተጋረጠባት ስለምትሆን÷ ስለ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ ይገባል። መስፈርቶቹ የሚገኙት በ1ኛ ጢሞቴዎስ ም 3 ቁ. 1-13 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።

1. "የማይነቀፍ" ይላል፤ ቤተክርስቲያንን ለነቀፋና ለክስ የማይዳርግ በሕይወቱ ዙሪያ ነቀፋ የሌለበት መሪ (አገልጋይ) መሆን አለበት፤
2. "የአንዲት ሚስት ባል" ፈት ያልሆነና በአንዲት ሚስት ጋብቻውን ያጸና እንጂ እየፈታ የሚያገባ መሪ እንዲሆን አልተፈቀደም። ይህ መመሪያ ዲያቆናትን ጨምር ያካትታል። ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ለሁሉም ክርስቲያን ያልተፈቀደ ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (አገልጋዮች) ይበልጥ አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይህ ካልሆነ ቤተ ክርስቲያንን ያስነቅፋሉ።
3. "ልከኛና ራሱን የሚገዛ" እነዚህ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁለት መስፈርቶች ናቸው። ራሱን የሚቆጣጠር ፣ የሚገዛ፣ በልክ የሚኖር፤

4. "እንደሚገባው የሚሠሰራ"፤ አገልጋዩን ሥራው (አገልግሎቱ) ይለካዋል። ስለዚህ ተግባሩን ሁሉ በአግባብና በሥርዓት የሚያከናውን መሆን አለበት።
5. "እንግዳ ተቀባይ"፤ እንግዳ ተቀባይነት በቤተ ክርስቲያን ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፤ የአንድ አገልጋይ መሥፈርት ሆኖም ተገልጸአል። ስለዚህ አገልጋይ እንግዳ ብቻ ሳይሆን እንግዳ ተቀባይም ሊሆን ይገባዋል።
6. "ለማስተማር የሚበቃ"፤ ቤተ ክርስቲያ ያለ ስብከት ልትኖር አትችልም። የቤተክርስቲያን መሥራች ክርስቶስ ኢየሱስ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ስበኩ።" (ማር.16÷15) ባለው መሠረት÷ ስብከት የአገልግሎት ሁሉ እንብርት ነው።
7. "የማይሰክር"፤ ስለመጠጥ አስከፊነት በመጽሐፈ ምሳሌ 23÷30-32 ያለውን መመልከቱ በቂ ነው። ጠጥቶ መስከር ኃጢአት ነው (1ቆሮ. 6÷10)። በተለይም መሪዎች ጠጪዎች ከሆኑ ቤተ ክርስቲያንንም ለነቀፌታ ይዳርጋሉና መስከር የለባቸውም። የቤተክርስቲያ አገልጋዮች ከምንነቀፍባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ስካር ነውና ልናስወግደው ይገባል።
8. "የማይጨቃጨቅ"፤ አገልጋይ ጭቅጭቅ÷ ንትርክ÷ ውስጥ የሚገባ ብሎም ለድብድብና ለአምባጓሮ የሚሰለፍ መሆን የለበትም።
9. "ገንዘብን የማይወድ"፤ ቀደም ሲል በሌላም እንደተመለከትነው ገንዘብ ለዕለታዊ ኑሮአችን አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ ፍቅረ ንዋይ ወይም ስግብግብነት

አስነዋሪ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ የእግዚአብሔርን መንጋ ለሚጠብቁት እረኞች "መጥፎን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት፤ ለመንጋውም ምሳሌ ሁኑ..." ያለው ስለዚህ ነው (1ጴጥ. 5፥2)።

10. "በውጭ ባሉት ሰዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው"፤ "ከመልካም ሽቶ መልካም ስም" እንደሚባለው (መክ. 7፥1) መልካም ስም፥ መልካም ማንነት ያላቸው አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያንን ከነቀፌታና ከጉዳት ስለሚጠብቁ፥ መሪዎች በዚህ መልካምነት የተመሰከረላቸው መሆን አለባቸው። "በውጭ ባሉት ዘንድ በአግባቡ እንድትመላለሱ" (1ተሰ.4፥12፣ ቆላ. 4፥5 መመልከት ይቻላል)።

በአጭሩ ቀንጨብ አድርጌ እዚህ ላይ ብገልጸውም ዝርዝር መስፈርቶችን በ1ኛ ጢሞ 3፥1-13፤ ቲቶ.1፥6-8 ውስጥ መመልከት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በቅዱስ መጽሐፍ በተገለጸውና በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን መመሪያነት መንገዝ ካልቻልን የቤተ ክርስቲያንን ህልውና አደጋ ላይ እየጣልን መሆናችንን መርሳት የለብንም። የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ትልቁ አደጋም ወግንና ሥርዓትን ብቻ የሚጠብቁ፥ የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ መመሪያና መንፈሳዊ መስፈርት የማያውቁና የሚጥሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት እየበረከቱ መምጣታቸው ነው። ብዙዎች ቄስና ዲያቆን የመሆን ጉጉትና ናፍቆት ያላቸው እንጂ ኃላፊነቱን በውል የሚረዱ አይደሉም። ችግሩ ደግሞ ከገጠር እስከ ከተማ የተንሰራፋ ነው። ቤተ መቅደስ ገብቶ መውጣትና ቅዳሴ፣ መቀደስ፥ ሰዓታት መቆም፥ ማሕሴት መቆም፥ ጸሎተ ፍትሐት ማድረስ የመሳሰሉት ላይ ብቻ ትኩረት ሲደረግ ይታያል። እያንዳንዱ ካህን ሥልጠና

አግኝቶ ኃላፊነቱን እንዲያውቅ የማድረግ ሥራ ብዙ አልተሠራም። አብዛኛዎቹ ምዕመናን፥ ለጥፋትም ይሁን ለሕይወት ወደ ሌሎች የእምነት ተቋማት ከሚፈልሱባቸው ምክንያቶች አንዱም ይኸው የአረኞቻችን መላላት ነው።

4.6. ክህነት በሀገራችን

ኢትዮጵያ በአማልኮተ እግዚአብሔር ሰፊ ታሪክ ያላትና በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት በግንባር ቀደምትነት የምትታወቅ ሀገር ናት። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ስምንት ላይ እንደተገለጸው ክርስትናን የተቀበለችውም በጃንደረባው አማካይነት በ35 ዓ.ም ነው። ይህም በክርስትና ቀደምትነቷን ያሳያል።

ክርስትና በኢትዮጵያ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በአባ ሰላማ ካሣቴ ብርሃን አማካይነት ይበልጥ መስፋፋቱን በርካታ የቤተ ክርስቲያንና የታሪክ ምሁራን ይስማሙበታል።

ሉሌ መልአኩ "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ" ቡተሰኘው መጽሐፋቸው "...የጢሮስ ተወላጅ ግሪካዊው ፍሬ ምናጦስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያደገ ስለነበረ ከኡራቱ ሊቀካህናት ከእንበረም ጋር ተመካክሮ የሚያስተምር የሚያጠምቅና የሚያቆርብ ጳጳስ ከአክሱም ለማምጣት ተላከ። ወደ አክሱምም የተላከ በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ በግሪክነቱ አልነበረም። የአክሱምም ፓትርያርክ አትናቴዎስም የኢትዮጵያን ቋንቋና ልማድ ስለምታውቅ አንተው ጳጳስና ሐዋርያ ሁን ብሎ ሰላማ በሚል ስም ማዕረገ ጵጵስና ሰጥቶ በ330 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው... እሱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንበረ ጵጵስናውን አክሱም ላይ አድርጎ በሀገራችን የወንጌልን ብርሃን በሰፊው ስለገለጸ ከሣቴ ብርሃን ተባለ። ከዚያም

በኋላ በፊት የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት የነበረውን ኢትዮጵያዊውን እንበረምን ሕዝበ ቀድስ የሚል ስም ሰጥቶ ኤጲስ ቆጳስ አድርጎ ሾመው። ... አባ ሰላማ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ በመሆን ... ለቀሳውስትና ዲያቆናትም ማዕርገ ክህነት ሰጠ። እንዲሁም የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ ከማድረጉም ሌላ ሐዲስ ኪዳን ከግሪክ (ከዮናኒ ከጽርዕ) ወደ ግዕዝ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር ተርጉሞአል።" ብለዋል። (ገጽ 123 እና 124)።

4.7. አሁን ያለው የክህነት አገልግሎት ምን ይመስላል?

አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አባ ሰላማን ጨምሮ በሌሎች የወንጌል ሰዎች (አባቶች) ጥረትና ትጋት ወንጌል እንዲስፋፋ በመደረጉ ቤተ ክርስቲያን እዚህ ደርሳለች። ስለ አባ ሰላማ የሕይወት ታሪክ ከላይ በትንሹ ቀንጨብ አድርጌ እንደአቀረብኩት "... ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያደገ ስለነበረ" ተብሎአል። የቤተ ክርስቲያን የመስፋፋት ሀልውናዋ ያለው እዚህ ላይ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስን "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍት አውቀሃል።" (2ጢሞ. 3፥15) እንዳለው ወንጌል ማለት የምሥራች ሆኖ በክርስቶስ የማዳን ሥራ ማመንና፥ መዳን ነው። ይህን የወንጌል ቃል ተምሮና አውቆ ያደገ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በእጅጉ ይጠቅማል።

ከቀደሙት አባቶቻችን ታሪክ የምንማረው ቁም ነገር ይኸው ነው። በወንጌል ያልተቀረጸ ትውልድ እያፈራን፥ በወንጌል

የተረከብናትን ቤተ ክርስቲያን ያለወንጌል እንዳናደርጋት፥ ከ1500 ዓመታት በፊት የወንጌል ብርሃን የበራላትንና የተስፋፋችውን ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ ማስፋፋት ሲገባን ጨለማ እንዳንሆንባት መንፈሳዊ መነሣሣትና ቁጭት ሊኖረን ይገባል።

በሀገራችን ያለውንና የነበረውን የክህነት ታሪክ ስንመለከት የሚያስደስትም የሚያሳዝንም፥ ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋትም ሆነ ውድቀት ምክንያት የሆኑ ካህናት እንደነበሩና እንዳሉም ይታወቃል። ከአባ ሰላማ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በየዘመናቱ ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት፥ ለወንጌል መዳረስ በጸም፥ በጸሎትና በአገልግሎት የሚተጉ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈሳዊ እውቀት እጦት ለዘላለም እዳይጠፉ ከልብ የሚያስቡ የመኖራቸውን ያህል ክህነትንና ሃይማኖትን መጠቀሚያና የዕለት ኑሮ መሻሻያ ብቻ አድርገውት ያለፉና ያሉም ይኖራሉ።

ለቤተክርስቲያን ዕድገት፥ ለወንጌል መስፋፋት ኖረው ያለፉትና ያሉት በረከታቸው ይድረሰን እያልን፥ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ በዘመናችን ለቤተ ክርስቲያናችን መስፋፋት እንቅፋት የምንሆን ካህናት ብንኖር ከነአባ ሰላማና መሰል አባቶች የሕይወት ታሪክ መማር ይገባናል።

4.8. ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት የካህናቱ ብቃት

ከገጠር እስከ ከተማ ያለችው "አሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን" መስፋፋት÷ ማደግ የምትችለው ካህናቱ "ክህነት" ምን እንደሆነ በትክክል ገብቶአቸውና የአገልግሎት ብቃት ኑሮአቸው ወንጌለ መንግሥቱን መስበክ÷ ማስተማር÷ ማስፋፋት ሲችሉ ብቻ ነው።

ቀድሰው ማቁረብ ብቻ ክህነት የሚመስላቸው በአንድ እጃቸው ዳዊት÷ በሌላው እጃቸው ዕውደ ነገሥት የሚይዙ ክህናት ወገን የመኖራቸውን ያህል÷ ከምዕመናን ወገንም በጓዳቸው ጨሌ÷ በራቸው ላይ ፀበል ያስቀመጡ፤ ጠዋት ቤተክርስቲያን÷ ከሰዓት በኋላ ጠንቋይ ቤት የሚሄዱ ብዙ ናቸው። "እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ?" (1ነገ. 18÷21) እንደተባለው በሁለት አሳብ ተጠምደው በማንክስ የሚኖሩ አሉ። ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው "አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን አስታግሥልን" በማለት እየጸለዩ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶችና ለሕዝባችን ወደ ሌሎች የእምነት ተቋማት መፍለስ ምክንያት የሆኑት የአንዳንድ ካህናት ጉዳይ ነው። "ዕውርም ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ" የሚለው ቃለ ወንጌል እንደዚህ ዓይነቶቹን ነው (ማቴ.15÷14)።

"... ያድን ዘንድ ወደማይችል አምላክ የሚጸልዩ እውቀት የላቸውም።" (ኢሳ.45÷20) ተብሎ እንደተጻፈው ከእውቀት ማጣት የተነሣ ከገጠር እስከ ከተማ ካለው ብዙ ሕዝብ መካከል ለልዩ ልዩ ከንቱ አምልኮ የሚገዛ ነው። እንዲህ ስቶ ለሚገኘው ሕዝብ ካህናቱ አለመድረሳቸው ደግሞ ከምንም በላይ አሳዛኝ ነው።

እስኪ በትንቢተ ኢሳይያስ 44÷6-18 ያለውን ደግሞ እንመልከት። "...የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል÷ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ÷ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው?...የዝግባን ዛፎች ይቆርጣል... ከእነርሱም አምላክ አብጅቶ ይሰግድለታል÷ የተቀረጸውንም ምስል ሠርቶ በእርሱ ፊት ይንበረከካል ... የቀረውንም እንጨት አምላክ አድርጎ ምስል ይቀርጽበታል፤ በፊቱም ተንንብቦ ይሰግዳል ወደ እርሱም እየጸለየ፡- አምላክ ነህና አድነኝ ይላል አያውቁም÷ አያስቡም፤ እንዳያዩ

ዐይኖቻቸውን÷ እንዳያስተውሉም ልቦናቸውን ጨፍነዋል።" የተባሉ አሕዛብ አሉ። ታዲያ በእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ያሉ ወገኖቻችንስ በየትኛው እምነት ወይም ክርስትና ወስጥ ነው የምንመድባቸው?

4.9. ስለ ቤተ ክርስቲያናን መስፋፋት ምን ያህል እናስባለን?

በገጠርም ሆነ በከተማ ካለው ሕዝባችን መካከል በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለአምልኮ ባዕድ የተጋለጠ ሕዝብ መኖሩ የሚካድ አይደለም። ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ከተሰለፉትና "አንቱ" ከተባሉት ካህናት መካከል ሳይቀር በዚህ ሥራ የተሠማሩ መኖራቸው ሊሰማ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ማስፋፋት ሳይሆን ማጥፋት እንደሆነ ይሰማናል።

አንድ ሰው ክርስቲያን ነው ከተባለ ከእንዲህ ዓይነቱ አጋንንታዊ ሥራ ፈጽሞ መራቅ አለበት። በአጠቃላይ አምልኮ ባዕድ ከሆኑ ልማዳዊና የቆዩ ተግባራት ሁሉ መላቀቅና በፍጹም ልቡ ወደ ፈጣሪው መመለስ እንዳለበት እናውቃለን።

ቤተ ክርስቲያን በተስፋፋችበት በሐዋርያት ዘመን የነበረውን ታሪክ ስንመለከትም ይህን እንረዳለን። "... አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናገሩ ይመጡ ነበር። ከአስማተኞች ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት፤ ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ። እንዲህም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።" ይላል (የሐዋ.ሥ.19÷18-20)። ቤተ ክርስቲያን ስትስፋፋ እንዲህ ዓይነት የመለወጥና የመመለስ ሁኔታዎች ይታያሉ። ቅራቅንቦ የሆኑ አጋንንታዊ የአስማት ሥራዎችና ልዩ ልዩ አምልኮ ባዕዶችን እንደ ታቀፉ ካህንነትም

ክርስቲያንነትም የለም፤ ቤተክርስቲያንን ማስፋፋትም በፍጹም አይቻልም።

በተለይ "ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል ስትመራ የነበረች ያለችና የምትኖር ሀገረ እግዚአብሔር" እያልን በምንተርክላት በእኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከላይ ያየናቸው የአምልኮ ባዕድ ሥራዎች መኖራቸው እጅግ እንድንቆጭና ሥር ሰዶ የቆየውን መጥፎ ታሪክ ለማስወገድ እንድንነሣሣ ሊያደርገን የሚያስችል መንፈሳዊ ሞራል ሊኖረን ያስፈልጋል። በተለይም ከጥቂት ዓመታት ወደዚህ የምእመናን ቁጥር ማሽቆልቆልና መቀነስ ሊቆጨንና በምን ምክንያት እንዲህ እንደሆነ ቆም ብለን ልናስብ የሚያስፈልገው ጉዳይ እንደሆነ ይሰማኛል።

● ቤተ ክርስቲያን የምትስፋፋው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ኢየሱስ ከሚያምኑ ከሁሉም የሰው ዘር እንጂ በአካባቢ በቋንቋ የተገደበች አለመሆኗን ቀደም ሲል ተመልክተናል (ራእ.5÷9-10)። ደቀመዛሙርቱን "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤" (ማቴ.28÷19፤ ማር.16÷15) በማለት ወደ ዓለም ሁሉ የላካቸው በሐዋርያት ትምህርት አምነው የተጠመቁት ሁሉ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባልና የመንግሥቱም ወራሾች እንዲሆኑ ነው። ቤተክርስቲያን የተስፋፋችውና የምትስፋፋው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነው።

ቤተክርስቲያንን ለማስፋፋት÷ ኢአማንያንን ለማሳመንና ወደ ክርስቶስ ለማምጣት አባቶቻችን ሐዋርያትና በየዘመናቱ የተነሡ ሊቃውንት ብዙ መሥዋዕትነትን ከፍለዋል። ይህን እውነት ያልተገነዘቡና ቤተክርስቲያን ማለት የልዩ ልዩ ሕዝቦች ስብስብ መሆኗን ያልተረዱ (ያላወቁ) አንዳንድ ወገኖቻችን÷ ቤተ ክርስቲያን በየሀገሩ የምትስፋፋበትንና የምትበዛበትን መንገድ በመዝጋት በአጉል ሃይማኖታዊ ቅናት ቤተክርስቲያንን የጠቀሙ መስለው እየጎዷት ያሉ ብዙዎች ናቸው።

● የቤተ እስራኤላውያን ታሪክ በቤተ ክርስቲያናችን ካህናት እይታ

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተችው በቤተ እስራኤል ነው። በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ምድር የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት በዓለም ሁሉ እየተስፋፋች አብያተ ክርስቲያናት እየተበራከቱ÷ የክርስቲያኖች ጎብረትም እየጨመረ÷ እያደገ መምጣቱን ከቅዱሳት መጻሕፍት መረዳት ይቻላል።

ቀደም ሲል እንዳየነው ክርስትናን በመቀበልና በማስፋፋት ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ የቀድመ ታሪክዋን የሚያደበዝዙ፣ ክርስቲያናዊ መስለው የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ተልዕኮ የሚያቀጭጩ ልማዶች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች መኖራቸው በተለያየ መንገድ የተነገረበትና የተገለጸበት ሁኔታ አለ።

በተለይም ከቤተ እስራኤል ጋር ከፍተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ትስስር ያላት ሀገራችን ብዙ እስራኤላውያን ያሉባትም ጭምር

ፍትና÷ ቤተ እስራኤላውያን ክርስቲያኖች ሆነው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለመስጠት እየፈለጉ እናንተ አትፈለጉም እየተባለ ተገልለው መኖራቸው ከየአቅጣጫው ሲነገር ይሰማል።

በኢትዮጵያ ስለሚገኙት ቤተ እስራኤላውያን መገለል÷ ጥላቻ÷ ስድብና ልዩ ልዩ ከበድ ያሉ የመከራና የሥቃይ ኑሮን እንደገፉ የሚያሳይና ዝርዝር ብሶት ያለበት÷ መስፍን አሰፋ የተባሉ ቤተ እስራኤላዊ የጻፉትን "አሊያህ ቤት" የተሰኘውን መጽሐፍ ከአንድ ወንድም እንደ አጋጣሚ አግኝቼው ተመልክቼው ነበር። ጸሐፊው የቤተ እስራኤላውያንን ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥና ከሰሜን ኢትዮጵያ እስከ ዋና ከተማችን አዲስ አበባ ድረስ ያለውን የጉዞ ሁኔታ÷ ቤተ እስራኤላውያን የሰፈሩባቸውን (የሚገኙባቸውን) አካባቢዎችንም በመጠቃቀስ ደርሶባቸዋል የሚሉአቸውን ችግሮች በሰፊው አትተዋል።

እኔም÷ ጸሐፊው ማንሣት የፈለጉት ጉዳይ በቤተ ክርስቲያናችን እይታ ምን ይመስላል? የሚለውን ነጥብ ማንሣት እፈልጋለሁ። ቤተ ክርስቲያን ማለት የልዩ ልዩ ሕዝቦች ስብስብ ናት ካልን የእኛ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ("ባለጅ ፈላሻ" ወዘተ..) እየተባሉ ሲናቁና ሲገለሉ÷ የነበሩ ቤተ እስራኤላውያን እንደ ማንኛውም ሰው በቤተ ክርስቲያን ጎብረት ታቅፈው እንዲያገለግሉ÷ እንዲገለገሉም የማይደረገው ለምንድነው?

ጸሐፊው ስለ ቤተ እስራኤላውያን "ቅስናና ድቁና አይቀበሉም... ቤተክርስቲያን ገብተው በማንኛውም የክህነት አገልግሎት እንዲሳተፉ ስለማይፈቅድላቸው ነው።" ብለዋል። "የክርስቲያን ሀገር" በምትባለው ሀራችን እንዲህ ዓይነት ኢክርስቲያናዊ ተግባር ሲፈጸም ማየትና መስማት ለእውነተኛ

ክርስቲያን ሁሉ አሳፋሪ ነው። ከቤተክርስቲያኒቱ በየጊዜው እየፈለሱ በሚሄዱት መቆጨት ሲገባን ከእናንተው ጋር እንሁን÷ እንቀድስ÷ እናገልግል÷የሚሉትን አንፈልጋችሁም÷ የእኛ ቤተ ክርስቲያን አባላት አትሆኑም ማለት የክርስቶስን ሞት ከንቱ ለማስቀረት እንደመሞከር ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው የተለያዩትን ሕዝቦች በደሙ አንድ ለማድረግ ነው (ኤፌ.2÷13-16)። ዓይኖቹን ወደ ሰማይ በማንሣት "ቅዱስ አባት ሆይ÷ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።" "ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ" በማለት ወደ ባሕርይ አባቱ ጸልዮአል (ዮሐ.17÷11 እና 20)። ይህም ጸሎቱ በእርሱ አምነው ስለሚከተሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የቀረበ ነው። "አንድ መንጋ ይሆናሉ፤ አረኛውም አንድ።" ያለውም ለዚህ ነው (ዮሐ.10÷16)።

ጌታ አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት ደሙን ሲያፈስ ጠላት ዲያብሎስ ደግሞ አንድነቷን ለማፍረስ ይተጋል። የቤተ ክርስቲያን አንድነት ምን እንደሆነ ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ታዲያ ሳይታወቃቸው በአጉል ቅናት ተይዘው የዲያብሎስ ጉዳይ አስፈጻሚ ሲሆኑ ይታያሉ። ይህን እውነት ያልተገነዘቡ ሰዎች ጸሐፊው እንደገለጹት በልማድ ፈላሻ የሚባሉት ወገኖች በቅዳሴ ጊዜ አብረው እንዳይቀድሱ በመከላከልና እንደ ልዩ ወገን በመቁጠር ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተክርስቲያን እንዳትስፋፋ ማነቆ ይሆናሉ። ከዚሁ ጋር የተያያዘ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በአንድ ሀገረ ስብከት ሥር የተፈጸመ አንድ ታሪክ ሰምቻለሁ።

ፈላሻ ከሚባሉት ወገኖች መካከል ቀሳውስትና ዲያቆናቱን "ከእኛ ጋር አብራችሁ አትቀድሱም" በሚሉ የአንድ አጥቢያ ቤተ

ክርስቲያን ካህናት መካከል በተፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት ጉዳዩ ከሀገረ ስብከት ጽ/ቤት እስከ ዞን መስተዳድር ጽ/ቤት÷ ከዚያም እስከ ክልል ጽ/ቤት ደርሶ ለብዙ ዓመታት እያጨቃጨቀ ብዙ ተደክሞበታል። በመጨረሻም በብፁዓን ሊቃነጳጳሳት መመሪያ ሰጪነትና ባርኮት "ፈላሻ" ለተባሉት ወገኖች ታቦት ተሰጥቶአቸው የራሳቸውን ቤተክርስቲያን እንዲተክሉ ተደርጎ ጉዳዩ በዚህ መንገድ ሊቋጭ ችሎአል።

በመጀመሪያው ፈላሻ ካልሆኑት ወገኖች መካከል ቀሳውስትና ዲያቆናት የሆኑት ፈላሻ የሆኑትን ወገኖች "በክህነት አገልግሎት ከእኛ ጋር አትሳተፉም" የሚል ጠንከር ያለ የልዩነት አቋም ይዘው በመነሣታቸው ምክንያት በሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ሥልጣነ ክህነታቸው ተይዞ ለረጅም ጊዜ ቆይተዋል። ነገር ግን ጉዳዩ በዳኝነቱም ሆነ በመንፈሳዊ ይዘቱ በቤተክርስቲያን ህልውና ላይ ያላተኮረ÷ ግላዊ ስሜትና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በሚመስል ሁኔታ ሥልጣነ ክህነታቸው የተያዘባቸው ሥልጣነ ክህነታቸው ተመልሶላቸው ልዩነታቸው ተጠብቆና ሁሉቱም ወገኖች በየግላቸው ቤራሳቸው ቤተክርስቲያን እንዲያገለግሉ መወሰኑ÷ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አመሠራረት ታሪክ የሚንድና እንደ ክርስቲያን ሆኖ ለሚያስብ ሰው የሚያሳዝን መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው።

ለዚህ ይመስለኛል "ኢየንድጋ ለሀገር..." እንደሚባለው ጉዳዩ የከነከናቸው የሀገረ ስብከቱ የስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ የሆኑት አባት (መጋቢ ምስጢር ገ/ሕይወት ኪዳነ ማርያም) በግላቸው ያላቸውን አቋም የምትገልጽ አንዲት አነስተኛ ጽሑፍ አዘጋጅተው የበተኑት። ከተበተነው ጽሑፍ መካከል አንዷን አንቀጽ ብቻ ከዚህ

እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ። የጽሑፍዋ ርዕስ "ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ።" ገላ. 3÷28 ትላለች።

"... ይሁን እንጂ በሀገራችን ያልተማረው ሕዝብ ቍርቶ ተማርን ብለው በልዩ ልዩ ማዕርግና የአገልግሎት ደረጃ ከሚገኙ ምሁራን ጭምር በስም አማንያን፤ በግብር÷ በአነጋገር ግን ኢአማንያን መስለውና አህለው የሚታዩ÷ የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ ባለመገንዘብ ከዘር ዘር በማበላለጥ አንዱን ዘር ቅዱስ ሌላውን ዘር እግዚአብሔር ያልመረጠው ርኩስ በማድረግ ክርስቶስ ለቤዛው የሞተለትን ምእመን ሲያበላልጡ ቆይተዋል። በተለይም በሀገረ ስብከታችን ውስጥ የሚገኙ የሽክላና የብረታ ብረት ባለሙያዎች ወገኖቻችን በሞያቸው ሊክበሩና ሊመሰገኑ ሲገባቸው ሙያዊ ስያሜያቸው ወደ ዘር ስያሜ ተቀይሮ "ባለጅ" እየተባሉ ሲነቀፉና ሲገለገሉ ኑረዋል። አሁንም አንዳንድ ምዕመናንና ካህናት ባለማወቅም ይሁን በሌላ ምክንያት በዚህ አስተሳሰብ እየተመሩ እነዚህን ክርስቲያን ወገኖቻችንን ከክህነት አገልግሎት ከቅዱሳት ምስጢራት ጭምር እንዳይሳተፉ እየከለከሉ በሥነ ልቦናቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደሩባቸው ይገኛሉ።" ሲሉ የተሰማቸውን ቁጭት ገልጸዋል።

ምንም እንኳ ጉዳዩ ከአቅማቸው በላይ በመሆኑና አጋር ከማጣታቸው የተነሣ መፍትሔ መስጠት ባይችሉም እንደ ስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊነታቸው እንደ ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ግን ድርጊቱን በይፋ ከመቃወም አልፈው አቋማቸውን በጽሑፍ አዘጋጅተውና በብዙ ኮፒ አባዝተው ለአካባቢው ካህንና ምዕመን እንዲሠራጭ ማድረጋቸው እጅግ የሚደነቅ ታሪካዊ ተግባር ነው።

ቢያንስ ለነገው ትውልድ ይህን የምስክርነት ቃላቸውን በጽሑፍ ማስቀመጥ ትልቅ የሐዋርያነት አሻራ እንደሆነ ይሰማኛል።

● ምን ዓይነት መንፈስ ነው?

ርእሰ ጉዳያችን ያዕቆብና ዮሐንስ የሰማርያ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበላቸው ምክንያት÷ "ጌታ ሆይ÷ ኤልያስ ያደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን?" ባሉት ጊዜ ጌታ ግን በመገሠጽና "ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" (ሉቃ.9÷51-56) ያለበትን ታሪክ እንድናስታውሰው ግድ ይላል።

እዚህ ላይ የደቀ መዛሙርቱ አሳብ ከጌታችን አሳብ ፍጹም የተለየ መሆኑን እናያለን። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ሁሉ በምሕረቱና በይቅርታው ከጥፋት ሊያድን የመጣ መሆኑን ዘንግተው ለሰማርያ ሰዎች ቁጣና ቅጣት ተመኝተላቸው። ጌታ ግን የተሳሳተ አሳባቸውን በማረምና በመገሠጽ ለሰው ያለውን ምሕረትና የመጣበትን ዓላማ ገለጸላቸው።

ያዕቆብና ዮሐንስ በራሳቸው አሳብ በመመራት ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ እስከ መዘንጋት እንደ ደረሱ ሁሉ በዘመናችን ያሉ÷ አንዳንድ ካህናትም ያወቁ መስለው ባለማወቅ ቀንበር ሥር በመውደቃቸው ምክንያት እየፈጠሩ ያለው ችግር ከፍተኛ መሆኑ የታወቀ ነው። ያዕቆብንና ዮሐንስን ጌታ እንደ ገሠጻቸው ቤተ ክርስቲያንን የጠቀሙ መስለው ቤተ ክርስቲያንን እየፈረሱ ያሉ ካህናትንም ሆነ ምዕመናንን በእግዚአብሔር ቃል ማረምና መገሠጽ የሚችል የበላይ ኃላፊ አስፈላጊ ነው። ይህ ካልሆነ

ግን ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነትና እድገት ራሳችን በራሳችን ጠላት እየሆን ነው። "እናገልግል" የሚሉትን እየገፋንና ቤተ ክርስቲያንን እያራቆትን መሆናችንን ተረድተንም በታሪክ ተወቃሾች÷ በእግዚአብሔር ፊትም ተጠያቂዎች ከመሆናችን በፊት አካሄዳችንን ማስተካከል ያስፈልጋል።

● የአንድነታችን ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩነትን በማስወገድና "የጥል ግድግዳ" የተባለውን፣ በእግዚአብሔርና በሰው÷ በሰውና በሰው መካከል የነበረውን ልዩነትን በሥጋው በማፍረስ አንድነትን መሥርቶአል። ይህም የሆነው "አንድን አዲስ ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው።" (ኤፌ.2÷14-16)።

የአንድነታችን ምስጢር ያለው እዚህ ላይ ነው። በክርስቶስ በሚያምኑት መካከል ትልቅ ትንሽ÷ ሀብታም ድሃ÷ አይሁዳዊ አረማዊ÷ ጨዋ ባሪያ የሚባል ነገር የለም (ቈላ.3÷10-11)። በክርስቶስ የተመሠረተው አንድነት ያልገባቸው ወገኖች ግን ባለማወቅም ይሁን ከደረሰባቸው መገለል የተነሣ ስለ አንድነት ማሰብ ይከብዳቸዋል። ልዩ ወገን ተደርገውና ተገልለው ከነበሩት ሳምራውያን መካከል አንዷ÷ ኢየሱስ "ውኃ አጠጪኝ" በማለቱ አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ ውኃ እንዴት ትለምናለህ? ስትል የጠየቀችው ለዚህ ነበር (ዮሐ.4÷7-26)።

ይህ ሁሉ ታሪክ ከተፈጸመ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ÷ ያውም በሠለጠነና የክርስትና ትምህርት በተስፋፋበት በዚህ ዘመን ከአንድ ጎጥ ተወልደው÷ አንድ ቋንቋ ተናግረው በሚኖሩና ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና በተቀበሉ አርቶዶክሳውያን መካከል "ልዩ

ወገን ናችሁ" ማለትና መባል በክርስትና ታሪክ እጅግ አሳፋሪና ኃላቀርነትም ነው። መንፈሳዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው አባቶች ይህን ለማስተካከል ጊዜው አላለፈም።

ካልሆነ ግን ታሪክ ይወቅሠናል÷ ትውልድም ይከሰናል። በግፍ የፈሰሰው የአቤልና የዘካርያስ ደም እንደ ጮኸ ሁሉ (ማቴ. 23÷35) ስለ ጽድቅና ስለ አንድነት በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደምም እርሱ ስለሞተባቸውና መገለል ስለሚደርስባቸው ወገኖች እየጮኸ መሆኑንና እኛም ተጠያቂዎች መሆናችንን ልናውቀው ይገባል።

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር አምላክ ማንም እንዲጠፋ የማይፈልግ መሆኑን እናውቃለን (ሕዝ.18÷32፤ 2ጴጥ.3÷9)። ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ከመንፈሳዊ እውቀት እጦት የተነሣ የጠፉ ሕዝቦችን ታሪክ በመጠኑ አይተናል። ለጥፋታቸው ምክንያት የሆኑት ደግሞ መንፈሳዊ መሪዎቻቸው (ካህናት) መሆናቸውን ቃሉን መሠረት አድርገን ተመልክተናል።

የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ስናነብ ከዚያ ውጪ ያሉ ሌሎች ጨምሮ ልዩ ልዩ ታሪኮችን ስንመለከትም በመንፈሳዊውም ይሁን በሌላው ጥሩ የሠራ ሁሉ ሲመሰገን መጥፎ የሠራ ግን ሲወቀስ ይኖራል። በተለይም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ መሆን አይቀርም። ዛሬም እያንዳንዳችን መንፈሳዊ መሪዎች (ከላይ እስከ ታች) ስለሰዎች መዳን ኃላፊነት አለብን። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ÷ በግዴለሽነትም ሆነ በሌላ ምክንያት መሥራት የሚገባንን ያህል ሳንሠራ (ሳናገለግል)

ብናልፍ ተጠያቂዎች ነን። ስለዚህ የሰዎች ጥፋት ግድ ሊለን ይገባል።

እግዚአብሔር በየዘመናቱ ሕዝቡን የሚጠብቁ መንፈሳዊ መሪዎችን አስነሥቷል። በማዕርግ ከፍና ዝቅ ማለት ቢኖርም የማገለግለው ሕዝብንና እግዚአብሔርን ነው ብሎ የሚያምንና ከህነታዊ ሥልጣን አለኝ የሚል ሁሉ በኃያሉ እግዚአብሔር ፊት ራሱንና አገልግሎቱን ቆም ብሎ ማየትና መፈተን ይገባዋል። ምናልባትም በእኛው አገልግሎት ምክንያት የጠፉና የባዘኑ ሕዝቦች (ምዕመናን) እንዳይኖሩና በደማቸው ተጠያቂዎች እንዳንሆን በተለይም ካህናት በጣም ልናስብበት ያስፈልጋል።

ገቢአችን ስላልተቋረጠ÷ ሙዳየ ምጽዋት ስልላነደለ ብቻ ቤተክርስቲያኒቱ ምንም የገጠማት ችግር እንደሌለ አስበን በዝምታ የምንቀመጥበት ጊዜ አይደለም። በሌለ ኑሮው ኑሮአችንን ሸፍኖ በክብር ለያዘን ሕዝባችን (ምዕመናን) አስፈላጊውን መንፈሳዊ አገልግሎት በተለይም የሚድንበትን ቃለ ወንጌል አስተምረን ከዘላለም ጥፋት ማዳን ይጠበቅብናል። ሌሎች ገንዘባቸውን ሳይቀር ሰጥተው ወደ ራሳቸው ለማፍለስ ሲጥሩ÷ እኛስ ወርቁንና ብሩን እየሰጠ የሚያገለግለንን ሕዝበ ክርስቲያን እንዳይበተን (እንዳይፈልስ) በቃሉ ሰብስበን መያዝ የለብንም ወይ? በየጊዜው ጊዜ ስለሚፈልሱት ምዕመናንስ ቁጭት የማይሰማን እስከ መቼ ነው? ለሁላችንም ማስተዋሉን ይስጠን።

አነሣሥቶ ላስጀመረኝ÷አስጀምሮም ላስፈፀመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው አሜን!

* * **ተፈፀመ** * * *

ዋቢ መጻሕፍት

1. መጽሐፍ ቅዱስ (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር) 1953 ዓ.ም
2. መጽሐፍ ቅዱስ (አ.መ.ት) 1993 ዓ.ም
3. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (የኢትዮጵያ መጽሐፍ) ካናዊ ማ/ቤት 1992 ዓ.ም
4. ጎርጎሪዮስ (አባ ሊቀ ጳጳስ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ት/ዘ/ማ/ቤት 1978 ዓ.ም
5. ሉሌ መልአኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ትንሣኤ ማ/ድርጅት) 1986 ዓ.ም
6. መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና በአማርኛ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማ/ድርጅት 1964 ዓ.ም
7. ቃለ ዓዋዲ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1991 ዓ.ም
8. መስፍን አሰፋ አሊያህ ቤት ግንቦት 2001 ዓ.ም
9. መዘምር ወ/ሩፋኤል (ቀሲስ) አምነትና በጎ ሕሊና ዕሴኒ ማ/ቤት 1999 ዓ.ም
10. መዘምር ወ/ሩፋኤል (ቀሲስ) የነፍስ አባትና የነፍስ ልጅ የመሆን ምስጢር ክፍል አንድ አፍሪካ ማ/ቤት 1996 ዓ.ም
11. መዘምር ወ/ሩፋኤል (ቀሲስ) የነፍስ አባትና የነፍስ ልጅ የመሆን ምስጢር ክፍል ሁለት ዕሴኒ ማ/ቤት 2001 ዓ.ም.

ለአስተያየትዎ

ቀሲስ መዘምር ወ/ሩፋኤል

ሞባይል፡ 0911-31-68-93

ፖስታ ሳ.ቁ. 80947

የአዘጋጁ ቀደምት ሥራዎች





“ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ።።

(ሆሴ. 4÷6)።።

“ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል፤ እረኞቻቸው አሳቱአቸው... የተቅበዘበዙ አደረጉአቸው፤”

(ኤር. 50÷6)።።

መጽሐፉን ማከፋፈል ለምትፈልጉና ለአስተያየታችሁ፡-

ሞባይል 0911-31-68-93

✉ 80947

ዋጋ 13.00 ብር